# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኦ.ትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ


# ትንሣኤ



እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ ከልጅሽ ከወዳጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ምሕረትን ለምኝልን ።


ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም　　ቁጥር 35　　ነሐሴ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.



www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

# ማውጫ

<u>አርእስት</u> ገጽ

ድንግል ማርያም የሁላችን መመኪያ ..................... ፫
ድንግል ዘወትር ..................................... ፬
ቤተ ክርስቲያንና ተግባሩ ............................. ፭
ከቤተ ክርስቲያን መዝገበ ታሪክ ....................... ፮
ጸመ ፍልሰታ ......................................... ፯
ከቋጥኝ ተፈልፍለው የተሠሩ አ ክርስቲያናት .......... ፰
ሴቶች በጾመ ፍልሰታ ................................. ፲
ደብዳቤዎች ........................................... ፲፪
ይህን ያውቁ ኖሯል? ................................... ፲፬
በደብረ ታቦር ክብሩን አየን ............................ ፲፭
ቤቴ የጸሎት እንጂ የንግድ ቤት አይደለም .............. ፲፮
ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ ........................... ፲፰
የአስም በሽታ ......................................... ፲፱
የምእመናን ድምፅ ...................................... ፳
ሊቃውንቶቻችን ........................................ ፳፩
ወጣቶች ............................................... ፳፪
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............................... ፳፭



የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ፱ኛ ዓመት በዓለ ሢመት በጸሎትና በታላቅ ሥነ ሥርዓት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ.ም. በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ይከበራል ።

www.ethiopianorthodox.org

# ርእሰ አንቀጽ

## ድንግል ማርያም የሁላችን መመኪያ

በዓለም ውስጥ ሰዎች የሚመኩባቸውና የሚታመኑባቸው ብዙ ነገሮች አሉ ። አንዳንዶቹ በታላላቅ ሰዎች ይመካሉ ። ሌሎች ደግሞ በሀብት በዘርና በቀለም ይመካሉ ። በመልክ ውበታቸውና በአካል አቅዋማቸው የሚመኩም አሉ ። ይህ ብቻ አይደለም ሰዎች በሠሩአቸው መሣሪያዎችና ዕቃዎች በእውቀታቸውና በጥበባቸውም የሚመኩና የሚታመኑ እንደአሉ ግልጥ ነው ። ይሁን እንጂ ሁሉም ነገር ሁሉን በእኩልነት አያስመካም ፣ ሁሉንም አያስተማምንም ። ምናልባት በሥጋዊ መንገድ አስተማማኝነት ቢኖረውም በመንፈሳዊ ሁኔታ ሊያስመካ አይችልም ። ነገር ግን በሥጋም በመንፈስም ሰዎች ሁሉ ያው ግን ክርስቲያኖች የሚመኩባት ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች የሆነች እርስዋም ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ።

የቀደሙን እንደአስተማሩን መጻሕፍትም እንደሚነግሩን ድንግል ማርያም የሁላችን መመኪያ ናት "የሁላችን" ማለት የወንዶችና የሴቶች የአይሁድና የአሕዛብ የሽማግሎችና የሕጻናት መመኪያ ናት ማለት ነው ። ሆኖም በክርስቶስ ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም ።

ቅድስት ድንግል ማርያም የሁላችን መመኪያ የሆነችበት ምክንያት በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጦአል ። ይህም እንደሚከተለው ነው ። ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከች ናት ፣ ለሌሎች በረከትን ለማሰጠት ከእግዚአብሔር ታላቅ መንፈሳዊ በረከትን ተቀብላለች ። ፍጹም ጸጋን የተሞላች ናት ፣ በዚህም የጸጋ ሙላት ለሌሎች ጸጋ ታሰጣለች ። ቅድስት ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት ለሰዎች የሚተላለፍባት ድልድይ ናት የሰዎች ልመናና ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የሚያርጉባት የእግዚአብሔር ምሀረትና ይቅርታ ወደ ሰዎች የሚወርዱባት መሰላል ናት ። ከዚህም ሁሉ በላይ እግዚአብሔር ወልድ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ሰው በመሆኑ የአምላክ እናት ሆናለች ። ይህም የመጨረሻው ጸጋ ስለሆነ የሰዎችን ልመና ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ ፍጹም ባለሙአልነትን ሊያሰጣት ችሏል ። በዚህም ባለሞአልነትዋ ምህረትን ለሰዎች ሁሉ ትለምናለች እግዚአብሔር ወልድ ከእርስዋ በነሣው ሥጋ ያዳነው ሕዝብ ለዘለዓለም እንዳይጠፋ ትጸልያለች ።

ይህ ሁሉ ጸጋና በረከት ባለሙአልነትም የተሰጣት ድንግል ከሰዎች ወገን እንጂ ከመላእክት የተገኘች አይደለችም ምድራዊት ፍጥረት እንጂ ኃይል አርአማዊት አይደለችም ። እንግዲያውስ ከፍጥረታት ሁሉ በላይ ፍጹም ክብር የተሰጣት ድንግል የባሕርያችን ክፋይ የሥጋችን ቁራጭ የአጥንታችን ፍላጭ በመሆንዋ እጅግ እንመካባታለን ።

ቅድስት ድንግል ማርያም "የሁላችን መመኪያ" ከመሆንዋም በላይ በተለይ ደግሞ የሴቶች መመኪያ ትባላለች ። ይህም ልዩ ምክንያት አለው ። በአይሁድና በክርስቲያን ዓለም ውስጥ ሞት በሴት/ በሔዋን/ ምክንያት እንደመጣ ይታመናል በዚህ ተቃራኒ ደግሞ ሕይወት ወይም ደኅንነት በድንግል ማርያም ምክንያት ሆኖአል ።በሔዋን ስህተት የገነት በር ተዘጋ በድንግል ማርያም ምክንያት ግን ተከፈተ በሔዋን ምክንያት መርገም ወደ ዓለም መጣ በድንግል ማርያም በኩል ግን ለዓለም በረከት ሆነ ። ይህና ይህን የመሰለው ሁሉ የሴቶች መመኪያ ያሰኛታል

ቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ ባሕርይ የአምላክ እናት እንደሆነች ለእኛም ለሁላችን የፍቅር የምህረትና የአደራ እናታችን ናት ፤ ስለዚህም በእርግጥ እንመካባታለን ፤ እናታችንም ከሆነች ዘንድ ለሁላችን ትራራለች ታማልዳለች አማላጅነትዋም አያሳፍርምና እንመካባታለን ።

www.ethiopianorthodox.org

# ድንግል ዘወትር

ድንግል ዘወትር (ባስልዮስ ሃይማኖተ አበው ፣ በስልዮስ ቅዳሴ ተመ) እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊት ድንግል ናት ። ድንግል በግእዝ ቋንቋ ጾታን የማይለይ ቅጽል ነው። ባለአገባቦች መድበል ቅጽል ይሉታል፡ ሁሉን የሚያጠቃልል ለማለት ነው ። የድንግልና ሕይወት ዋና መመሪያው ወንዱ ከሴት ፣ ሴትዋ ከወንዱ ተለይተው ሳይቀራረቡ ንጽሕናቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ ነው ።

ከብሉይ ኪዳን በፊት በዚህ ሕግ የተመሠረተ ድንግልናዊ ሕይወት መኖር አለመኖሩ ግልጥ ሆኖ አይታወቅም በ.ብሉይ ኪዳን ግን አልፎ አልፎም ቢሆን ከነቢያት እንደ እነ ኤልያስ እንደ እነ ዮሐንስ መጥምቅ ያሉ ደናግል ነበሩ ። ስለ ሴቶች ደናግል በብሉይ ኪዳን ተደጋግሞ የሚነገረው ባል እስኪያገቡ ድረስ ያሉትን ልጃገረዶች ብቻ ነው ፣ የጋብቻ ዕድሜያቸው ደርሶ ያገባሉ ፣ ደናግል መባላቸውም ይቀራል ። ከዚህ በቀር በብሉይ ኪዳን በድንግልና መላ ዘመናቸውን ስለኖሩ ሴቶች የተጻፈ የለም (Virgo Intacto) (ቨርጎኢንታክቶ)

በኢሳይያስ 7፡14 ላይ "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ፣ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች" ተብሎ ትንቢት የተነገረላት ቅድስት ድንግል ማርያም ግን በስምም በግብርም ከእነዚህ የተለየች ናት ፣ ዘለዓለማዊት ድንግል ናትና ። ሊቃውንትም ቅድመ ፀኒስ ጊዜ ፀኒስ ድኅረ ፀኒስ ቅድመ ወሊድ ጊዜ ወሊድ ድኅረ ወሊድ ድንግል መሆንዋን መስክረውላታል ።

ድንግል ማርያም ለደናግል በማይስማማ ጠባይ እናትነትዋ ሲነገር ለወላጆች በማይስማማ ጠባይ ደግሞ ያለ ተፈትሖ መውለድዋ ዕፁብ ይባላል ልጅዋ



ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም

"አምላክ ወሰብእ" አምላክም ሰውም ሲባል እንደሚኖር እስዋ ደግሞ "ድንግል ወእም" እናትም ድንግልም ትባላለች አምላክን መውለድዋ ወላዲተ አምላክ መባልዋ የብቻዋ እንደሆነ የዕንስዋም የመውለድዋም ሁኔታ አስደናቂ ምሥጢር ነው ።

ስለ ድንግል ማርያም ድንግልና ስንናገር ድንጋሌ ሥጋ ብቻ አይደለም ድንጋሌ ሕሊናም የተሰጣት ናት ድንጋሌ ሥጋ ከገቢር ማለት ከመሥራት መለየት ሲሆን ድንጋሌ ሕሊና ደግሞ በሐሳብ አለመባከን ክፉ አለመመኘት ነው። ስለዚህ "ድንግል በሕሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ ድንግል በክልኤ" በሁለት ወገን ድንግል እንላታለን ።

የእመቤታችንን ድንግልና በመጀመሪያ የተቃወሙ አይሁድ ናቸው ልጅዋን የዮሴፍ ልጅ ካሉት እስዋን የዮሴፍ ሚስት ማለታቸው ነውና ። ቀጥሎም በመጀመሪያ መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ገደማ የነበሩ ግኖስቲኮች ኤቢዮኒቶችና ሌሎችም መናፍቃን ፣ ግማሾቹ እንደ አይሁድ ሐሜት በዘር በሩካቤ ወልዳዋለች ሲሉ ፣ ሌሎቹ ደግሞ በድንግልና ፀንሳ መውለድዋን ቢያምኑም እሱን ከወለደችው በኋላ ሌሎች ልጆችን በሩካቤ ወልዳለች እያሉ በክንቱ ያሚት ነበር ። እነዚህም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ አንዲ -ዲኮ-ማሪያቶስ (አንጢድቁ ማርያጦስ) የሚባሉት ናቸው ።ፍቹም ፀረ ማርያም ማለት ነው (ሃይ.አበው)

ይህ የማርያም ጠላቶች ሀሳብ በዘመናት ሁሉ ውስጥ ውስጡን ተጉዞ መጥቶ አሁንም በቤተ ክርስቲያን ሁከትን ሲያቀጣጥል ይታያል ። ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ብዙ ሰዎች እንደ አይሁድና እንደ ግኖስቲኮች የእመቤታችንን የድንግልና ዶግማ ያቃልላሉ ። እነዚህ መናፍቃን ለተሣልቋቸው (ለፌዛቸው) የሚጠቅሱት (ማቴ.12፡46 ማር.3፡31-35 ።ሉቃ. 8፡19-21 ። ምዕ.13፡55) ያሉትን ንባቦች ነው ። ወንድማማችነት በዕብራውያን ልማድ በእናት ልጅነት ብቻ አይደለም የአክስት የአጎት ልጅ የወንድም የእኅት ልጅ ሁሉ ወንድም እኅት ይባላል ። (ዘፍጥ. 13.8) በዚህ የቋንቋ ልማድ ወንጌላውያን ከክርስቶስ ደቀመዛሙርት ጥቂቶቹን "አኃዊሁ" ወንድሞቹ እያሉ ጽፈዋል ። የቋንቋውን ጠባይና አገላለጡን የማያውቅ ግን ቸኩሎ አስተያየት ከመስጠት ቢቆጠብ ከስህተት ይድናል ።

ሌላው ለሀሳባቸው ደጋፊ መስሎ የሚታያቸው ንባብ በማቴ.1፡25 እና በሉቃ.2.7 ያሉት ንባቦች ናቸው ። እዚህም ላይ ቢሆን የቋንቋውንና የአገላለጡን ሁኔታ ማጤን ከስህተት ያድናል ።በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ "በኩር" የሚለው ንባብ የመጀመሪያ ልጅ ማለት አይደለም ፣ ክርስቶስ በኩር መባሉ የመብት የልዕልና ስሙ ነው ። ክርስቶስ በኩር ሲባል በሁለት ክፍል ነው።(ሀ) ስለ ቅድመ ዓለም ህልውናው ፣ (ቆላ. 1፡15) ለ በኩረ ምውታን በመጀመሪያ ሞትን የገደለ ሁለተኛም የማይሞት ስለሆነ (ራእ. 1፡5)

ስለ እመቤታችን ድንግልናዊ ሕይወት ሊቃውንት ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል ብዙ ምሳሌዎችንም አቅርበዋል ። ስለ ክርስቶስ ማንነት በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ዶግማ ከመናፍቃን ጋር ብዙ እንደ ተከራከሩና እምነታቸውንም እንደአስከበሩ ሁሉ ስለ እመቤታችንም የወሰኑት "ቅድመ ፀኒስ ጊዜ ፀኒስ ድኅረ ፀኒስ ቅድመ ወሊድ ጊዜ ወሊድ ድኅረ ወሊድ" ከመፅነስዋ በፊት በፀነሰች ጊዜ ከፀነሰች በኋላ ከመውለድዋ በፊት በወለደች ጊዜ ከወለደች በኋላ ማኅተመ ድንግልናዋ አለመለወጡን ነው። ይህን ዶግማ መወሰናቸውና በዚህም የተነሣ ከፀረ ማርያሞች ጋር መከራከራቸው በግፊት በማያውቁት ጉዳይ አልነበረም። በመጻሕፍተ ነቢያትና በመጻሕፍተ ሐዲሳት የተጻፉትን አዛምደው አገናዝበው ተርጉመው ነው። ለምሳሌ በሕዝቅኤል ራእይ 44 1-2 በርሳ ይከፍት ገብቶ በር ሳይከፍት የወጣውን ጕልማሳ መሢሕ ወልደ አብ ወልደ ማርያም እንደሆነ ሲተረጉሙ በመግባቱም ሆነ በመውጣቱ ጊዜ ያልተከፈተችው እልፍኝ ደግሞ የዘለዓለማዊት ድንግል የእመቤታችን ምሳሌ መሆንዋን በሰፊው ገልጠዋል (ኤፍሬም)

በመጻሕፍተ ሐዲሳት (ማቴ. 1፡18 ። ሉቃ 1፡34 ለምልክት የተነገሩት ቃላት በመንፈስ ቅዱስ ያለ ተፈትሖ መፅነስዋን በግልጥ ሲያስረዱ ገና በዕንስ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆንዋ የተነገረላት ንግሥተ ሰማያት ማርያም ከወለደችም በኋላ ከነበረችበት የድንግልና እርከን ዝቅ እንዳላለች በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ ግልጥ ነው ። ከዚህም ሁሉ ጋር ዓለምን ያዳነው ልጅዋ በመስቀል ላይ እንዳለ በመጨረሻ የተናገረው "ነዋ ወልድኪ ነያ እምከ" እነሆ ልጅሽ እነኋት እናትህ የሚለው የአደራ ቃል ለእመቤታችን ከርሱ በቀር ሌላ ምንም እንዳልነበራት ያስረዳል ። ሌላ ልጅ ቢኖራትማ ለተማሪ በአደራ መች ይሰጣት ነበር? (ዮሐ. 19፡26)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የማይለወጥ ድንግልና የምታስተምረው ትምህርት የምታምነው እምነት ይህ ነው ። ይህን ትምህርትዋን እምነትዋን የሚያስተባብሉ ቢኖሩ ሳትሰለች መላልሳ ታስረዳለች ።

ወትረ ድንግል ማርያም
ወትረ ድንግል ማርያም
ወትረ ድንግል ማርያም

ጸሎታ ወበረከታ ወምሕረተ ፍቁር ወልዳ የሀሉ ምስሌነ ።
ለዓለመ ዓለም ።

አባ ጎርጎርዮስ
የሸዋ ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ ኤ'ም ·ኦ

## ክርስቲያንና ተግባሩ

ክርስቲያኖች ከሌሎች በምን ይለያሉ ? እያሉ ብዙ ሰዎች አልፎ አልፎ አንዳንድ አስተያየት ይሰነዝራሉ ክርስቲያንነት በተግባር የማይገለጽ ከሆነ አስተያየቱ ሊሰነዘር የሚገባው ነው ። አልፎ አልፎ የሥራ ሳይሆን የስም ክርስቲያን ነን በሚሉ በአንዳንድ ሰዎች ላይ የቅድስና ምልክት አይታይባቸውም ይህም ጥፋቱ ከሰዎች እንጂ ከሃይማኖቱ ስላይደለ አነጋገሩ ትክክል ነው ሊባል አይገባም ።

ክርስቲያኖች ከሌሎች የሚለያዩበት ምን መሆን አለበት? ክርስቲያኖች ከሌሎች ከሌላው የሚለዩበትና የመንፈስ ለውጥ የሚያገኙበት ምን ሊሆን ይገባል? ለነዚህ ነገሮች መልሳቸው እንደሚከተለው ይሆናል። ክርስቶስ ከሚሠሩ ክርስቲያኖች ጋር ይኖራል። ክርስቲያኖች ከእሮ ጋር ይኖራል። ክርስቲያኖች ከአሮጊው ሕይወታቸው ወደ አዲሱ ሕይወት ለመለወጥ ቁርጥ ውሳኔ ሲያደርጉ ክርስቶስ ወደ ልባቸው ስለሚገባ የመንፈስ ለውጥ ያገኛሉ ። ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ፡ አሮጌው ነገር አልፏል ፡ እነሆ ሁሉም ነገር አዲስ ሆኖአል" ይላል ። 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕ. 5 ቁ 17 ይህ ከሆነ የመንፈስ ለውጥ እንዳለ ተረጋግጧል ። በዚህ አኳኋን ክርስቲያኖች ለራሳቸውም ብቻ ሣይሆን አርአያነታቸውን ለሌሎች ማሳየት ይገባቸዋል ።
ምናልባት እነዚህ ተግባሮች የሚያስቸግሩ መስለው ይታዩ ይሆናል ። ይህም ማለት ምሳሌነቱን በምን ሁኔታ ማሳየት እችላለሁ በቤቴ በአካባቢየና በመቤቴ ላሉ ሰዎች እንዴት እመሰክራለሁ ትሉ ይሆናል ። እነዚህን መፈፀም ቀላል እንጂ ከባድ አይሆንም ። ይህንንም ለማድረግ የሚረዱ አራት መፍትሄዎች እናቀርባለን ። 1ኛ በአለባበስ 2ኛ በአነጋገር ፣ 3ኛ በሥራና በአካሄድ

ወደ ገጽ ፳፮ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ከቤተ ክርስቲያን መዝገበ ታሪክ

መስከረም (1972 ዓ.ም)

1 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የዘመን መለወጫን በዓል ምክንያት በማድረግ በበዓሉ ዋዜማ በሬድዮና በቴሌቪዥን ቃለ ምእዳን አስተላልፈዋል ። ባስተላለፉትም ምዕዳን በሀገር ለታወጀው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ቤተ ክርስቲያን ባላት ኃይል ሁሉ በዘመቻው እንድትሳተፍ ገልጸዋል ።

2 በዚሁ ወር የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን በይበልጥ ለማጠናከር በአዲስ አበባ ከተማ በአምስት ቦታዎች ከፍተኛ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲቋቋም አድርገዋል ።

3 መስከረም 17 ቀን 1972 ዓ.ም. የቅዱስ መስቀልን በዓል በአብዮት አደባባይ አክብረዋል ።

4 በ30 1972 በሀይ ካህናት ማሰልጠኛ ት/ቤት በሙያ ማሻሻያ ኮርስ የሰለጠኑ ካህናትን መርቀው የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል ።

ኅዳር

5 ኅዳር 14 ቀን 1972 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የንዋየ ቅድሳትና ቅርሳቅርስ መምሪያን ጐብኝተው የሥራ እርምጃው ከአሁን በበለጠ እንዲሻሻል የሥራ መመሪያ ሰጥተዋል ።

6 በ18 2 72 የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ መልእክተኞች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በጐበኙበት ወቅት መልእክተኞችን ተቀብለው አነጋግረዋል የመታሰቢያ ስጦታም አድርገዋል ።

ታህሳስ

7 ታህሣስ 1 ቀን 1972 ዓ.ም ቅዱስ ሲኖዶስ የዓመቱን የመጀመሪያውን ስብሰባ ሲጀምር ጉባኤውን በጸሎት ከፍተዋል።በጉባኤው ፍጻሜ ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሆነ ውሳኔ ተላልፎ አል ።

8 በ20 4 72 ወደ ፊት ስለሚቋቋመው መንፈሳዊ ኮሌጅ በመንበረ ፓትርያርክ አዳራሽ ቅዱስነታቸው በተገኙበትውይይት ተካሒዷል ።

9 ከታህሣስ 23-25 72 ዓ.ም በብፁዓን ጳጳሳት በዝዋይ ማሰልጠኛ በተደረገው ስብሰባ በ5 ሀገረስብከቶች የካህናት ማሠልጠኛ ት ቤቶች እንዲከፈቱ የተደረገውን ጥናት ቅ ፓትርያርኩ አጽድቀዋል ።

10 ታህሳስ 27 ቀን 72 ዓ.ም የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት ምክንያት በማድረግ ለምእመናን ቃለ ምእዳን አስተላልፈዋል ፤ በዓሉም የሰላምና የደሕንነት በዓል መሆኑን አብሥረው በዚሁ ዓመት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከበረውን የሕፃናት እንክብካቤ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ በመሆኑ ከፍተኛ ትብብር የምታደርግ መሆንዋን ገልጠዋል ።

ጥር

11 ጥር 4 ቀን 72 ዓ .ም ሦስት ኢጲስ ቆጶሳትን ሾመዋል ። በ11 5 72 ዓ.ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማት ኮሚሽንና በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ለሚቀጥሉት 3 ዓመታት የልማት ፕሮግራም በአፍሪቃ አዳራሽ ውይይት ተካሒዶአል ።

12 በዚሁ ቀንና ወር የዓለም ክርስቲያኖች የጸሎት ቀን በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በኢትዮጵያ የሚገኙ የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና አባላት በተገኙበት በታላቅ ድምቀት ተከብሮአል በዕለቱም የዓ. አ. ክ. መልዕክተኞች ተገኝተዋል ።

13 ጥር 11 ቀን 1972 ዓ.ም ቅዱስ ፓትርያርኩ በተገኙበት በጃን ሜዳ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀት ተከብሮአል ።

14 በ29/5/72 ቅዱስ ፓትርያርኩ በወሊሶ ከተማ የምትገኘውን ደብረ ምጥማቅ ቅድስት ማርያምን ጐብኝተው በመምሕር ወ/ተንሣይ ግዛው አጥማቂነት የተፈወሱትንና የሚፈወሱትን ሕሙማን አጽናንተዋል ።

15 የካቲት 2 ቀን 1972 ዓ.ም. በዓተ ዓቢይ ጾምን ምክንያት በማድረግ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ቃለ ምዕዳን አስተላልፈዋል ።

16 የካቲት 12 ቀን 72 ዓ.ም በግፈኛው የኢጣሊያ ፋሽሽት የተገደሉትን የኢትዮጵያውያን ሰማዕታት 43ኛው ዓመት መታሰቢያ በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በተከበረበት ወቅት ቅዱስ ፓትርያርኩ በብሔራዊያን ሰማዕታት መካነ መቃብር ላይ የአበባ ጉንጉን አኑረዋል ።

17 በ20 6 72 ቀደም ሲል የዓለም ዓብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በደቡብ አፍሪካና ሮዲሺያ ይፈጸም ስለነበረው የዘር ልዩነትና ጭቆና የዓለም ክርስቲያኖች ሁሉ አቅዋም እንዲወስዱ ባስተላለፈው - መሠረት የኢ.. ኦ. ተ. ቤ. ክ ከላይ በተጠቀሰው ቀን የዘር ልዩነትንና ጭቆናን በማውገዝ አቅዋም ወስዳለች ።

መጋቢት

18 ከመጋቢት 24 ቀን 1972 ዓ.ም ሚያዝያ 14 ቀን 72 ዓ.ም ድረስ ቅ. ፓትርያርኩ ኢየሩሳሌምንና ግሪክን ጐብኝተዋል በኢየሩሳሌም በቆዩበት ወቅት ስለደሬር ሱልጣን ገዳም ጉዳይ ከሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግረው ጉዳዩ በሰላም የሚያልቅበትን መንገድ አስፈጽመው ተመልሰዋል ።

19 መጋቢት 27 | 1972 የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ለጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ቃለ ምእዳን አስተላልፈዋል ።

ሚያዝያ

20 ብቅዱስነታቸው ሊቀመንበርነት የሚመራው ሲኖዶስ ከሚያዝያ 22 ቀን 72 ዓ.ም-ግንቦት 14 ቀን 72 ዓ.ም ድረስ ባደረገው ስብሰባ ተፈላጊና ወቅታዊ ውሳኔዎችን አስተላልፎአል ካሳለፋቸው ውሳኔዎች በድርቅ ለተጐዱ ወገኖች እርዳታ እንዲሰጥ 1 ሃይማኖት አበው ፣ 2 የወጣቶች አጠቃላይ ጉባኤ ፣ 3 ተምሮ ማስተማር እየተባለ ይጠራ የነበረው ሁሉ በወጣቶች ጉዳይ መምሪያ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል



# ጾመ ፍልሰታ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች የሚፏቸው ሰባት አጽዋማት አሉ። ከሰባቱ አንዱ የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ፍልሰት (ዕርገት) ምክንያት በማድረግ ምእመናን ጽሙዳን ሆነው ከጣመ ከላመ ምግብና ከአልኮል መጠጥ ተከልክለው ጥሬ ቆርጥመው ውሃ ጠጥተው የሚጾሙት ጾመ ፍልሰታ ነው ። ይህን ጾም ከሌሎች አጽዋማት ለየት ያለ የሚያስመስለው የሕፃናት መጾምና ወደ ሥጋ ወደሙ መቅረብ ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች የሆኑ ሁሉ ከሕፃናት እስከ ሽማግሌዎች ጾመ ፍልሰታን ይጾማሉ ፤ ከዚህም የተነሣ "በፍልሰታ የማይጸድቅ አቦን የማይጠምቅ" የሚል ምሳሌ አበው አለ ። በተለይ በጾመ ፍልሰታ ሕፃናት ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል የሚያደርጉትን መንፈሳዊ እሽቅድምድም የሚመለከት ሁሉ ኢትዮጵያውያን ምእመናን በድንግል ማርያም ላይ ያላቸውን ፍጹም ፍቅር ሊረዳ ይችላል ።

የጾመ ፍልሰታ ይዘት በሌሎች አብያተ ክርስቲያን እንዴት እንደሆነ ለማወቅ የተለያዩ የአብያተ ክርስቲያን ካህናትን ጠይቀን የሰጡንን አስተያየት በዚህ እትም አውጥተናል ።



ግሪካዊው ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ ጴጥሮስ

1ኛ በኢትዮጵያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ስለጾም የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል ። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይላሉ ሊቀ ጳጳሱ ጾም ሁለት ትርጉም አለው ፣ ይህም ሥጋዊና መንፈሳዊ ነው ። ሥጋዊው ትርጉም ከተለየ የምግብ አይነት ለተወሰነ ጊዜ መከልከል ነው ። መንፈሳዊ ትርጉሙ ግን ከማናቸውም ክፉ ነገር መከልከል ነው እንደቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አነጋገርም ዋናው የጾም ሽክም ከክፋት ሁሉ መራቅ ነው ። መዝሙረኛው በዓቢይ ጾም ጊዜ የሚከተለውን መዝሙር ይጠቅሳል "ጌታችን ለማስደሰት. እንድንችል በመንፈስ እንጹም"

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከምግብ የመከልከል ጾምን ሳትነቅፍ መንፈሳዊውን ጾም ታጠብቃለች ሰውንም ወደ እግዚአብሔር በይበልጥ የሚያቀርበው ይህ አይነቱ ጾም ነው ። ጾም ሰውን ከጌታ ጋር አንድ የማድረግ ትርጉም አለው. ከምግብ የመከልከል ጾም ዋና አላማ ሰው በጠባዩ እንዲታረም በመንፈሳዊ ነገር እንዲጠነክርና ለምግባረ ሠናይ ብቁ እንዲሆን ነው ። ጾም ክፉ ነገርን ሁሉ ለመከላከል የሚያበቃ መሣሪያና ወደ ድል የሚያመራ መንገድ ነው ፡ ብለዋል ።

2ኛ በኢትዮጵያ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህን አባ ዘካርያስ



ካቶሊካዊው ካህን አባ ዘካርያስ

በኢትዮጵያ ያለች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ጾመ ፍልሰታን ለተከታዮችዋ ታስተምራለች ታጾማለች ። የጾሙ ይዘትም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተለየ አይደለም ። ቢሆንም ሕፃናት ቅብዓተ ሜሮን(ኮንፈርሜሽን) እስኪፈጸምላቸው ድረስ ማለት አሥራ ሁለት ዓመት እስኪሆናቸው ምሥጢራትን አይካፈሉም ።

በዓለም ያለች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የምሥራቅና የምዕራብ ተብላ ከሁለት ትከፈላለች ። ስለሆነም የምሥራቅዋ የምሥራቁን ፣ የምዕራብዋ የምዕራቡን ባህል ትከተላለች ። በኢትዮጵያ ያለችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ተከታዮችዋ ኢትዮጵያውያን እንደመ መሆናቸው መጠን ኢትዮጵያዊ ባህል ኢትዮጵያዊ ሥርዓት አላት ። ነገር ግን ይላሉ አባ ዘካርያስ በደቡብ ኢትዮጵያ ያሉ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያን ላቲናዊ ባህልና ሥርዓት ለመከተል ይሞክራሉ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ምዕራብና ደቡብ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ባህልና ሥርዓት ያልተስፋፋ ስለነበረ በዚያ በኩል የገቡሚስዮናዊያን የላቲኑን ባህልና ሥርዐት ስለአስተማሩ ነው።ይሁን እንጂ እኛ አንስማማበትም ምእመናኑም አይደሰቱበትም ምእመናኑ የሚደሰቱ ኢትዮጵያዊ በሆነ ባህልና ሥርዓት ሲገለገሉ ነው።ስለሆነም በኢትዮጵያ ያለችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጾመ ፍልሰታን የምትጾመውና በዓለ ፍልሰታን የምታከብረው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ባልተለየ ሁኔታ ነው ። በአውሮፓ ወይም በላቲን ባለችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጾሙ አይታወቅም ግን በዓለ ፍልሰትዋ በውሳኔ ይከበራል ብለዋል ።

3ኛ ፋዘር ሻኬ በኢትዮጵያ ለ14 ዓመታት ያህል የኖሩና ከ3 ዓመታት በፊት ጀምረው በአዲስ አበባ የሚገኙትን የሕንድ ክርስቲያኖች የሚመሩ ሕንዳዊ ካህን ናቸው ፣ እርሳቸውም በሰ

ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ከቋጥኝ ተፈልፍለው የተሠሩ
# ጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያን በጎጃም ክፍለ ሀገር

ታሪክ ያለው ትውልድ በታሪኩ ይኮራል ፤ ታሪክም ከእናት ሀገር የተገኘ ክብር ስለሆነ የእናት ሀገሩን ልዕልና የበለጠ ይጠብቅል ፤

በመሆኑም ታሪክ የሚያስመሰክርለት ከትውልድ የወረሰው ቅርስ በመሆኑ በሥጋና አፅም የወረሰውን ዜግነት ከፍተኛ ቅድሚያ እንደሚሰጠው ሁሉ ከእናት ሀገሩ የተላለፈለትን ቅርስና ጥንታዊ ታሪክም ከዚህ ባላነሰ ሁኔታ ሊያከብረውና ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ።

የእናት አገሩን ቅርስና ታሪክ የማያከብር ዜጋ ካለ የወላጅ እናቱን ጡት እንደመንከስ የሚያስቆጥር ነውና ከእንዲህ ዓይነት ተግባሩ ለመመለስ አሁኑኑ ንስሐ መግባት አለበት እንላለን ።

ይህ መሆኑ ከታወቀ ዘንድ በአባቶች ጥረት የተላለፈው ባህሉን የማክበር ፡ ቅርስን የመጠበቅ ፤ ዓላማ በዛሬው ትውልድም አድሮ ጠቃሚ ባህልንና ቅርስን ለሌሎች ለማስተዋወቅ ለተከታዩ ትውልድም ለማስተላለፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ ካላደረገ የብዙ ሺህ ዐመታት ታሪክና ቅርስ አለኝ ብሎ ማውራቱ በቂ ሊሆን አይችልም አዲሱ ትውልድ ጠቃሚውን ባህልና ጥንታዊ ቅርሱን ለመጠበቅ ከምንጊዜውም የበለጠ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት የነቃና የተደራጀ ዜጋ አይዘነጋውም ።

አንዳንድ አገሮች ለረጅም ጊዜ የቆየና ያልተዳቀለ ባህል ስለሌላቸው የየሀገራቸውን ባህልና ቅርስ በምርመራ ለማግኘት የኤኮኖሚያቸውን አካፋይ እንደሚመነዝሩ የታወቀ ነው ።

በኢትዮጵያ ግን በየኤውራጃዎቿ ጥቅጥቅ ባለው ደኖቿዋ እንኳ ሳይቀር ለብዙ መቶ ዓመታት ምንም ዓይነት ጥበቃና ጥንቃቄ ወይም እድሳት ሳይደረግላቸው እንደዋዛ ተገትረው የሚታዩት ጥንታውያን ቤተ መንግሥቶች አብያተ ክርስቲያናት ሀውልቶች ዓምዶች የባዕዳን ምራቅ በጉምጀታ የሚያዝረበርቡ በመሆናቸው ምንጊዜም ልንኮራባቸውና ልንመካባቸው ይገባል ።

ታዲያ ጥንታውያን ቅርሶቻችን ቀደም ሲል አስፈላጊው ጥበቃና ጥንቃቄ ሳይደረግላቸው ከመቅረቱ የተነሣ እንደ ቀላል ዕቃ ባልባሌ ቦታ ሾልከው እየወጡ ለባዕዳን በመሸጣቸውና በሌላ በኩልም ወዳጅ መሳይ ጠላቶች ከባህር ማዶ በማሻገር የባዕድ አገሮች ቅርስ ማዳበሪያ ያደረጉዋቸው እጅግ ብዙዎች በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ወደውጭ አገር ሄዶ ቤተ መጻሕፍቶችንና መዘክሮችን የጐበኘ ኢትዮጵያዊ ዓይኑን ጣል ካደረገ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቅርሶች የባዕድ ሀገር ቅርስ መደጐሚያና ማስከበሪያ መሆናቸውን ይመለከታል ።

ይህ ብቻም አይደለም ፤ ከሀገራችን መሬት ያልወጡት ጥንታዊ ቅርሶቻችን ዛሬም ቢሆን ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ሲደረግላቸው አይታይም ። ብዙ መቶ ዓመታት ያሳለፉ ዕጹብ ድንቅ የሚያሰኙ ጥንታውያን ቅርሶቻችንን ሱቅ በደረቴዎች በሌላ በኩልም የቅርስ ቀበኞች እንበላቸው ግምታቸው ይህ ነው የማይባሉትን ቅርሶች በቀላል ዋጋ አሳልፈው በባዕዳን ሲሸጡ ማየቱ ለእውነተኛ ኢትዮጵያዊ አዲስ ትውልድ ምን መስሎ ይታየው ይሆን?

ቀን በቀን የውጭ ዜጋዎች የትራፊክ መብራት ባቆማቸው ቁጥር እንኳ ሳይቀር በግድ ግዙን እየተባሉ መተላለፊያ ማጣታቸውን ስንመለከት አሁንም ስለ ቅርሶቻችን ጥንቃቄ አለማድረጋችንን ያረጋግጣልና ባይሆን ስንኳ ይሉኝታ ፈርተን ብናስብበት መልካም ነው ።

ስለዚህ የትናንቱ ለዛሬ የዛሬው ለነገ ካላደረ ቅርስ አይሆንም ኢትዮጵያን የሚያሳውቋት ጥንታውያን ቅርሶቻችን በየቀኑ ሲነጉዱ ዝም ብሎ መመልከቱ ተገቢ አይደለም የሚመለከታቸው ክፍሎች ተሰባስበው ያስቡበት እላለሁ ። ለዚህ ሁሉ አባባል ሌላ በቂ ምክንያት አለ ። በሽህ የሚቆጠሩ ዓመታት ዕድሜ ያላቸው ጥንታውያን የብራና መጻሕፍትና ስዕሎች በአጋጣሚና በአንዳንድ ጥቃቅን መደለያዎች በተለከፉ የቅርስ ቀበኞች እየተመዘበሩ በየግለሰቦች ቤት መቀመጥ የማይገባቸው ጥንታውያን ቅርሶች በ1969 ዓ.ም. ፀረ ሕዝቦችን ለማጋለጥ በተደረገው አሰሳ በየቦታው መገኘታቸው በወቅቱ በመገናኛ ዘዴዎች ለሕዝብ መገለጡ ቅርሶቻችንም ምን ያህል እንደወደሙ በቂ ማስረጃ ነው ።

ከነዚህም ውስጥ ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ ቢያስፈልግ ከ960 ዓመታት በላይ ዕድሜ ያላቸው የብራና መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ስዕሎች በአሰሳው ከአንድ ግለሰብ ቤት በመገኘታቸውና ለጊዜውም የእኔ ባይ በመጥፋቱ ወደ 2ኛ ፖሊስ ጣቢያ የተወሰደው ለብዙ ጊዜ በዕስር ቆይተዋል ።

እነዚህ መጻሕፍት በ1969 ዓ.ም.በሌጐስ ጠቅላላ የጥቁር ሕዝቦች ባህል በታየበት ወቅት በቁም እስርነት ወደ ሌጐስ ተወስደው እያንዳንዳቸው ለኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳልያ አስገኝተው የተመለሱት ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት ቅርሶቻችን ምንም ዓይነት እንክብካቤና ጥበቃ ያልተደረገላቸው መሆኑን በይፋ ያመለክታል ። ይኸውም ከሌጐስ ተመልሰው ወደእስር ቤት መግባታቸው በቂ ምስክር ሊሆን ይችላል ።

ከሌጐስ ተመልሰው ወደ እስር ቤታቸው ቢገቡም በፖሊስ ጣቢያው ባሉ አንዳንድ ተቆርቋሪ ዜጋዎች ጥቆማ በ1971 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ወደሚመለከታቸው ክፍሎች ቢወሰዱም ሌሎች በዚሁ ዓይነት ያሉ ቅርሶች ስለአሉ አሁንም ለዚህ ዓይነቱ ተግባር ይመለከተኛል አይመለከተኝም በማለት ሳንወስን እያንዳንዳችን ወደ መጥፋት የተቃረቡትን ጥንታውያን ቅርሶች ጠብቆ ለማቆየት ኢትዮጵያዊነታችን ያስገድደናል ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን ሁሉ ለምሳሌ ያህል ጠቀስን እንጂ የግራኝ ደንጋይ ያጤ ፋሲል ቋጥኝ ወዘተ እየተባለ እንደዋዛ በየቀኑ በከብት እረኞች እየተሰባበረ የሚቀረውንና በመሰባበርም ላይ ያለውን ጊዜው ይቁጠረው ።

የዛሬው ጽሑፋችን መነሻ ከዚሁ ባልተለየ ሁኔታ ያለምንም ጥንቃቄና ጥበቃ ስለአሉት በ12ኛው ምዕት ዓመት ማለትም ከዛሬ 800 ዓመት በፊት በንጉሥ ላሊበላ ዘመን እንደታነፁ የሚገመቱ አብያተ ክርስቲያናት አስደናቂ ታሪክ ነው ።

ታሪኩም እንዲህ ነው ። የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚር. በሚያደርገው ታሪካዊ ቦታዎች ፍለጋ ለጥፋት የተቃረቡ ሁለት ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትና ሁለት ቤተ መንግሥቶች በየካቲት ወር 1972 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ አግኝቶአል ።

በጐጃም ክፍለ ሀገር በባህር ዳር አውራጃ በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ በተለይ ደንጋይ ደበሎ ማርያም እየተባለ የሚጠራው ቦታ አካባቢ ስለተገኙት ሁለት ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ከቦታው ድረስ ሄደን የተመለከትነውንና በተለይም በዚሁ ክፍለ ሀገር የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚር. መ ቤት ኃላፊ ጓድ መኰንን ተሰማ ጭምር ታሪኩን እንዳስረዱን ቀጥለን እናቀርባለን ።

### 1ኛ ደንጋይ ደበሎ ማርያም

ከባህር ዳር ከተማ ሃያ ስድስት ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘው የደንጋይ ደበሎ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ይህም በቅርስ ፍለጋ የተገኘ ነው ።

ይህ የደንጋይ ደበሎ ማርያም የዋሻ ቤተ ክርስቲያን ከስምንት መቶ ዘመን በላይ የተቀመጠ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑ የሚገኘው ከትልቅ ዋሻ ውስጥ ነው።

ቤተ ክርስቲያኑን ከመሬት ፈልፍሎ ያሠራውም ቅዱስ ላሊበላ ነው ይባላል ይህ አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን ላዩ መሬት ለብሶ ፤ ውስጡ ግን ዋሻ ሆኖ አሁንም መንፈሳዊ አገልግሎት የሚከናወንበት ሥርዓተ ቅዳሴም የሚፈጸምበት ነው ።

ታዲያ ይህ አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን ከመሬት በታች ሆኖ በላዩ መተላለፊያ መሬት ስለአለና ላዩ ስለሚታረስ ከታች በጫካና በዱር የተዋጠው ቤተ ክርስቲያን መኖሩ ከአካባቢው ሕዝብ በቀር ሌላ አያውቀውም ።

ይህ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ላሊበላ በላስታ የሚገኙትን አስራአንድ ቤተ መቅደሶችን ከመሥራቱ በፊት ያሠራው እንደሆነ ሲገመት በዚሁ ቦታ የጀመረውን አስደናቂ ሥራ ያቋረጠው በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ሊግባቡትና ቀና መንስም ሊያሳዩት ባለመቻላቸው እንደሆነ በአካባቢው የሚገኙ አረጋውያን ይናገራሉ ።

ቤተ ክርስቲያኑ በክፊል ከመግቢያው በር ጀምሮ በነጭ ኖራ የተሠራ ጥንታዊ ቤት ከዋሻው መግቢያ ላይ ሰባት በሮችና ሶስት መስኮቶች ያሉት ሲሆን ይህኛው የተሠራው በዓፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ተረጋግጦአል።

ይኸውም የቅዱስ ላሊበላ በ12ኛው ምዕት ዓመት የተሠራ ሲሆን የዓፄ ሱስንዮስ ደግሞ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ሆኖ የላሊበላ ከ800 መቶ በላይ እድሜ ሲኖረው የአፄ ሱስንዮስ ደግሞ 300 ዓመታት ሆኖታል ። ይህ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ይቀደስበታል ። የአካባቢው ነዋሪዎች በመተዳደሪያ ችግር ምክንያት ቤተመቅደሱን ለማስጠገን ባለመቻላቸው ከዋሻው በር የተሠራው ቤት ጣሪያ ከዋሻ ጋር በተገናኘበት በኩል ውሃ በማፍሰሱ ምክንያት መጠነኛ የሆነ ጉዳት በሕንፃው ላይ ሊያስከትል ከመቻሉም በቀር በአሁኑ ሰዓት ሕንፃው በደኅና ሁኔታ ላይ ይገኛል ። ወደፊት በዚሁ ከቀጠለ ግን የውሃው ፍሳሽ ያሰጋዋል ።

2ኛ ግንብ ጊዮርጊስ ቤተ መንግሥት ከባህር ዳር ከተማ 45 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘው ግንብ ጊዮርጊስ ከሚባለው ስፍራ አልፎ አልፎ በመናድና በመበላሸት ላይ ያለ ሕንፃ ይገኛል ። ይህ ግንብ የተሠራው ደግሞ በዓፄ ሱስንዮስ መሆኑን በአካባቢው ያሉ አረጋውያን ይናገራሉ ።

ሁኔታው በጣም አስደሳችና አስገራሚ የሆነው ይህ ጥንታዊ ግንብ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ 150 ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን በደቡብ ሰሜን 130 ሜትር ርዝመት አለው ።

የሕንፃው አሠራር ከፍታው ሰባት ሜትር ሆኖ (አልትትዩድ 2300 ይሆናል) አሠራሩ አራት ማዕዘን ከመሆኑም ሌላ ይህ ሁኔታ የሚያሳየው የጎንደሩ ክብ ሲሆን ይህኛው ግን አራት ማዕዘን ሆኖ ለየት ማለቱን ነው ።

እንዲሁም ይኸው ግቢ አጥሩ በዚያው አይነት ግን ዙሪያውንን የአጥሩ ግንብ ግን ዙሪያውን በመናድ ላይ ነው ።

አልፎ አልፎ የእንቁላል ሥራ ፍራሽ በግማሽ የተፈነከተ ይታይበታል ። ከዚህም ሌላ በመሀከል ያለው የዋናው ቤተ መንግሥት ቤቱ በአፈል ተንዶ ቁጥቋጦ ያበቀለ ዘጠኝ ክፍል ልዩ ልዩ በር ያላቸው ክፍሎች ሲሆን በቅርብ ያለመብራት ለማየት ያዳግታል ።

በውስጥ ደግሞ ስምንት የተለያዩ ክፍሎች ይገኛሉ ። ይህ ቤተ መንግሥት ለብዙ ዘመናት የቆየ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ይገኛል ። ምክንያቱም የተሠራው በዓፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ነው ። አካባቢው መውደም ሲጀምር በአካባቢው የሚገኙት ገበሬዎች በአጠቃላይ ግቢውን ያርሱታል በግንቡም ሥር እያስጠጉ ስለሚጠቀሙበት በመሸርሸርና አፈሩ በመበላት በየቦታው በመናድ ላይ ነው አሁንም ለብዙ ጊዜ የእርሻ ቦታ ሆኖ በመኖሩ በጣም በአስጊ ሁኔታ ላይ ከመገኘቱም ሌላ ምንእልባት በቅርብ ጊዜ ፈጽሞ የመፍረስ እድል እንዳይገጥመው ያሰጋል ።

### 3ኛ ቤተ ማርያም ሕንፃ

ይህ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ተሠርቶ የነበረው በዓፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ቤተ መንግሥቱ በተሠራበት ጊዜ ነው ቤተ ክርስቲያኑም የዓፄ ሱስንዮስ የማስቀደሻ ሕንፃ እንደነበረ ይነገራል ሕንፃው በአሁኑ ጊዜ ሲታይ አሠራሩ አስደናቂና አስገራሚ እንደነበረ ሲያስረዳ

ወደ ገጽ 16 ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ሴቶች በጾመ ፍልሰታ

ሴቶች በጾመ ፍልሰታ ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ያደርጋሉ ከነዚህም ጥቂቶቹን ብንጠቅስ በፍስክ ሲጠቀሙበት የቆዩትን የቤት ቆሳቁስ እቃን ለውጠው የጾም ምግብ የሚያቀርቡበትን እቃ ያዘጋጃሉ ። በተጨማሪም የሚበላውን የምግብ ዓይነት ያሰናዳሉ ። ልጆቻቸውን ራሳቸውንና በጠቅላላም ቤተሰቦቻቸውን ለጾሙ እንዲዘጋጁ ያደርጋሉ ።

ከዚህም በኋላ ጾሙ ሲጀመር ሱባኤ ገብተው በቀን አንድ ጊዜ ብቻ እየበሉ የሚጾሙት እናቶች ወደተለየ ቦታ ተሰማርተው ሱባኤያቸውን ይጀምራሉ ። ሌሎቹም በየአጥቢያቸው ወደ ሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ጥዋት የውዳሴ ማርያም ትርጉም ለመስማት ሲገሰግሱ እንደገና የቤታቸውን ሥራ አከናውነው ሲያበቁ ጸሎተ ቅዳሴ ለመከታተል ይሄዳሉ በቢሮ ሥራ የሚውሉት ሴቶችም ቢሆኑ እንደዚሁ ጥዋት ጸሎታቸውን አድርሰው ወደ ሥራቸው ይሄዳሉ ቀንም ወደየ አቅራቢያቸው አብያተ ክርስቲያናት በመሄድ ያስቀድሳሉ ። ከዚህም ሌላ ሴቶች የፍልሰታን ጾም ምክንያት በማድረግ ማታ ማታ ልዩ ልዩ ምህላዎችን ቤተሰቦቻቸውን ሰብስበው በዜማ ያደርሳሉ ።

ከነዚህም ምህላዎች ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን ።

1ኛ ‘‘እ ማርያም እለምንሻለሁ ባሪያሽ
አንድ ጊዜ ስሚኝ ቀርበሽ ባጠገቤ ቆመሽ ፤
የዓለምን መከራ ያየሽ
ብዙ ጉዳይ አለኝ ላንቺ የምነግርሽ
እ ቸሪቱ ተመላለሽ
ሌሊት በሕልሜ ንገሪኝ ቀርበሽ
አደራሽን
እጄን በእጅሽ ያዥኝ እንዳልባንን
በሰጊድ ሰላም ።

ይህም ማለት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የዓለምን መድኃኒት ክርስቶስን በወለደችበት ጊዜ ሄሮድስ ክርስቶስን ለመግደል ሲያሳድዳት ልጅዋን ይዛ እንደተሰደደችና ብዙ መከራ ደርሶባት እንደነበር ሲያመለክት ይህች ድንግል ክርስቶስን የወለደች ርህርህት አዛኝ በመሆኗ የሰው ልጆችን መከራ ቻል የማትል ከልጅዋም የምታማልድና ምህረትን የምትለምን መሆኗን የሚያመለክት ሲሆን በትህትና ሰላምታ እና ቀርብልሻለን እያሉ እናቶች በፍልሰታ ጾም ማታ ማታ እየደጋገሙ ያዜሙታል

2ኛ ‘‘ከሁሉ ሁሉ ጤፍ ታንሳለች ፤
ከጭቃ ወድቃ ትነሳለች
ከዚያች ጤፍ
የአዳም ልጅ ሁሉ አትስነፍ
የአዳም ልጅ ሁሉ ሰነፈና
የኑሮ ቤቱን እረሳና ፤
ተው አትርሳ ተው አትዘንጋ ፤
ተሰርቶልሃል የእሳት አልጋ ፤
ያን የእሳት አልጋ የእሳት ባህር
እንደምን ብየ ልሻገር
ተሻገሩት አሉ የሰሩት ምግባር
እኔ ባርያሽ እንዴት ልደር ።
በሰጊድ ሰላም ይላሉ ።

ትርጉሙም ከላይ እንደሚያስረዳው ሁሉ አንዲ የጤፍ ፍሬ ከማንኛውም አዝርእት ያነሰች እንደሆነች የታወቀ ነው። ሆኖም ይህች አነስተኛ ጤፍ በዘር ወራት ተዘርታ ከጭቃ ላይ ወድቃ ሳትቀር ገለባ ለብሳ አንዲ ብዙ ሆና ትነሳለች በዚህ አንፃር በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩት የአዳም ልጆች ግን ከዚያች ከአነስተኛዋ ጤፍ አንሰው የዘለዓለም ቤታቸውን እረስተው ከፈጣሪአቸው የታዘዙትን ትእዛዝ ዘንግተው በዚህ ዓለም ተድላና ደስታ ተታለው ትንሣኤ ሙታንን በማስታወስ ንስሃ ሳይገቡ በድንገት ሞት እንዳይደርስባቸውና ወደ ዘለዓለማዊ እሳት እንዳይገቡ የሚያስረዳ ነው እናቶችም ይህንን እያስታወሱ እንዲህ ያለው እድል እንዳይገጥመን ቅድስት ድንግል ሆይ ከልጅሽ አማልጅን እያሉ በትጋት ይጸልያሉ ።

3ኛ ‘‘የኢየሩሳሌም ወራዙት
ጌታችንን ወሰዱት
ምን ሊሉት
ግንድ አሸክመው ሊያጋፉት
እኔን ያጋፉኝ
ሃሰት በቃሉ ላይገኝ በሰጊድ ሰላም የሚል ነው ።

ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ልጆች ድህነት ሲል ወደዚህ ዓለም መጥቶ በአይሁድ እጅ መውደቁንና የእኛን ሃጢአት በመስቀል ተሰቅሎ ሊደመሰስልን የሚሰቀልበትን ግንድ እንዳሸከሙትና በእኛም ምክንያት እንደ ሃጢአተኛ ተቆጥሮ ጸዋትወ መከራ መቀበሉን ያስታውሳል ።

እንግዲህ እነዚህን ከአንድ እስከ ሦስት ተራ ቁጥር ያቀረብናቸው ምህላዎች ለምሳሌ ያህል ነው እንጂ ይህንን በመሰለ መንገድ የሚሄዱ በጣም ብዙ ምህላዎች እንዳሉ የታወቀ ነው ።

አዎ ሴቶች በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ያላቸው ፍቅር ከፍ ያለ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው ። ፍቅራቸውን ከሚገልጹበት አንዱና በቂ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችል ሴቶች ሆነው የማርያም ዝክር (ማህበር) የማያደርሱ ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው ለማለት እንችላለን ። ከዚህም ሌላ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማችን ብዙ ልማዶች የሚታዩባት ስለሆነች ከተማሩት ሴቶች በስተቀር እናቶች የማርያም ቀን ማለትም በየወሩ በ21ኛው ቀን ጽዋ ይዘው ስእለ ማርያምና መሶበወርቅ ተሸክመው የታቦት ጥላ አጥልተው ሲሄዱ በየመንደሩና መንገዱ በብዛት ይታያሉ ። ታዲያ ይህንን የጠቀስነው ጥሩ ልማድ ነው ብለን ሳይሆን በድንግል ማርያም ላይ ሴቶችም ያህል ፍቅር እንዳላቸው ለመግለጽ ያህል ነው ።

ይህም ፍቅር በተለይ በሴቶች ላይ ሊያይል የቻለው በሔዋን ጥፋት ተዘግቶ የነበረው የገነት በር በቅድስት ድንግል ማርያም አማካኝነት ስለተከፈተ ነው ስለሆነም ‘‘ቅድስት ማርያም የሴቶች መመኪያ ናት’’ተብላ ትጠራለች በዚህ ምክንያትም የፍልሰታን ጾም በተለይ ሴቶች በታላቅ አክብሮት ተቀብለው ይጾማሉ ህጻናት ልጆቻቸውንም እንዲጾሙ ያበረታታሉ ።

እዚህ ላይ እንግዲህ ሴቶች ይህንን ጾም የሚጾሙት ከላይ በተጠቀሰው ሁናቴ ብቻ ነው? ወይንስ ከሃሜት ከምቀኝነት ከቅናት ከዝሙት ርቀው ንስሃ በመግባትም ጭምር ነው የሚል ጥያቄ በያንዳንዱ አእምሮ ይኖር ይሆናል ።

አዎ ለዚህ ማስረጃ የሚሆን ስለ አንዲት እናት ትምክህት እንገልጻለን ።በአንዲት ገዳማዊት ቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢ በሚገኝ በአንድ ክፍል ቤት ውስጥ አንዲት መነኩሲት እናትና አንድ ትንሽ የቆሎ ተማሪ ሱባዔ ገብተዋል በዚህ ጊዜ እማሆይ ትንሽ እንቅልፍ ሸለብ አድርጎአቸው እንዳለ ተማሪው የሚያስፈልገውን ጸሎት በሙሉ አድርሶ ተኝቷል ። በዚህ ጊዜ እማሆይ ከእንቅልፋቸው ነቅተው እሳታቸውንእያያይዘው እየሞቁ የፍልሰታ ምህላቸውንና ሌላውን ጸሎታቸውን አድርሰው እንዳበቁ ጌታ ሆይ ይህ ተማሪ እንደ እኔ አይጸልይምእያሉ ብቻቸውን ሲናገሩ ተማሪው ሰምቶ አይ እማማ አይድከሙ በነገር ሥራ የሚገባበት ቤት አይደለም አላቸው ይባላል ።

እንግዲህ ጾም የምንጾመው ምህላ የምናደርሰው የምንጸልየው ሁሉ ለይስሙላ ሳይሆን በንጹህ ህሊና በትሁት ልቡና ሆኖ ከእግዚአብሔር ዋጋ እንድናገኝበት እንጂ ሰው አይቶ እንዲያመሰግነን ወይም እንዲህ ጾምኩ ፀለይኩ ብለን ልንመካበት አይደለም ።

ብዙዎቻችን ከሰዎች ጋር ተጣልተን ቂም በልቡናችን ይዘን የበደሉንንም ሆነ የበደልናቸውን ይቅር ሳንል ንስሃ ሳንገባ ለውዳሴ ከንቱ ጾም በመጣ ቁጥር ቆሳቁስ እቃዎችን በፈላ ውሃና በእቃ ማጠቢያ መርዝ ይታጠባሉ እኛም አስቀዳሾች ሆነን ሽብ ረብ እንላለን ።ብዙዎችም አይ እነ እከሌ እኮ ጸድቃን ናቸው ሳያስቀድሱ አይበሉም ይሉናል እግዚአብሔር ግን ምንም እኛ በባዶ ብንደክም ፊትን ሳይሆን ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ስለሆነ ጾማችንን ብቻ ሳይሆን ሁለመናችንን ይመረምራል

ስለዚህ ስንጾም በሰዎች ዘንድ ለታይታ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ እንደምናገኝበት አድርገን እንጹም ጾም ከሌሎቹ ትእዛዛት ጋር ተሟልታ ከተገኘች የነፍስን ቁስል ትፈውሳለችና ።

ብርሃን ተድላ

## ከቋጥኝ የተሠሩ ...

ከገጽ ፱ የዞረ

የቦታው አቀማመጥም ከዚሁ ከግንብ ጊዮርጊስ ቤተ መንግሥት ስምንት መቶ ሜትር ራቅ ብሎ የሚገኝ ነው ።

ይህም ቤተ ክርስቲያን ከሞላ ጐደል ብልሽት ቢኖረውም በአሁኑ ጊዜ ምዕመናን አይጠቀሙበትም ሥርዓተ ጸሎትም ሆነ ቅዳሴ አይከናወንበትም ቤተ ክርስቲያኑ በተለይ የተጐዳው የጣሪያውና የመዝጊያው ሥራዎች በከፊል ሲሆን ጥንታዊነቱን እንደያዘ በሚያስደስት ሁኔታ ላይ ይገኛል ።

ቢሆንም መፍረስ ጀምሯል ቦታውንም ቁጥቋጦና ደን አልብሶታል ገብቶ ለመመልከት እንኳ አስቸጋሪ ነው ይህ ቤተ ክርስቲያን ወደፊት ከፍተኛ ወጭ ከመጠየቁ በፊት አሁኑኑ ጥገና ቢደረግለት በአነስተኛ ወጭ ተጠግኖ የጸሎት ሥራ ለመጀመር የሚያስችል መሆኑ ታምኖበታል ።

ስለዚህ የሀገረ ስብከቱ ቤተ ጽሕፈት ከባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚ..ጋር ተባብሮ አስቸኳይ ጥገና ቢደረግ ይህን የመሰለ አኩሪ ቅርስ ከጥፋት የሚድን መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመጠቆም እንወዳለን ።

በተለይ አስቸኳይ የመንገድ ጠረጋ ቢደረግለትና ገበሬዎችም ከብት እንዳያስግሩበት ቢሆን መልካም መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እናሳስባለን ።

4ኛ ይባባ ተክለ ሃይማኖት ግንብ ፤

በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ይባባ ከሚባለው ቦታ ያለው ጥንታዊ ሕንፃ ዳግሞ የዓፄ ፋሲል መኖሪያ ቤተ መንግሥት እንደነበረ ተረጋግጦአል ። ይህ ቤተ መንግሥት የተሠራው ከእንቁላል ግንብ ሲሆን አሠራሩም በሌሎች ከተሞች እንደሚገኙት የዓፄ ፋሲል ቤተ መንግሥቶች ተመሳሳይነት ያለው ነው እንቁላል ግንቦቹም ልዩነት የላቸውም ።

ይህ ቤተ መንግሥት በብዛት እየፈራረሰ ሲሆን በተወሰኑ ማዕዘኖች ብቻ ግንቡ ቁሞ ይታያል ።

በዚህ ቤተ መንግሥት ዙሪያ ዓፄ ፋሲል ያሠራው ቤተ ክርስቲያን እንዳለ የሚነገር ሲሆን ለጊዜው ግን አልተገኘም ።

ስለዚህም ቤተ ክህነት ከባህል ሚ.. ጋር ተባብሮ ይህንንም ደን የለበሰ አካባቢ መንጥሮ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲገኝ ጥረት እንዲያደርግ አጥብቀን እንጠይቃለን ።

ሪፖርቱን ለማግኘትና ቦታውንም ተ

ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ደብዳቤዎች

ይድረስ ለትንሣኤ መጽሔት
አዘጋጅ
አዲስ አበባ

መጀመሪያ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ። ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በትክክል እንደምትመልሱልኝ እተማመናለሁ ።

1 ከባሕረ ሐሳብ ቀጥሎ ባለው የድሜጥሮስ ታሪክ ላይ ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ ድሜጥሮስ በነበሩ ምዕመናን ዘመን የአጽዋማትና የበአላት አወጣጥ የተወሰነ ባለመሆኑ እሱ በተሾመ በ27 ዓመት ጌታችን ባረገ በ207 ዓመት በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት በዐቢይ ቀመር በመዕከላዊ ቀመር በንዑስ ቀመር ወስኖ የበዓላትንና የአጽዋማትን አወጣጥ የዘመንን አቆጣጠር አወጣ” ይላል ይህንን የዘመን አቆጣጠር እኛ ብቻ ነን ወይስ ሌላም ሐገር ይጠቀምበታል? ከተጠቀሙበትስ ለምን የኛ ዘመን አቆጣጠር ከሌሎቹ ተለየ?

2 በየዓመቱ በኢየሩሳሌም የሚከበረውን የትንሣኤ በዓል የኢትዮጵያ ምዕመናን የሚያከብሩት ከውጭዎቹ ጋር በአንድ ቀን ነው ወይ? ካልሆነ ለምን ተለያየ?

3 በግዕዝ ቋንቋ እኛ ግዕዝ እዝል እንዲሁም አራራይ እያልን እንደምንጠራው የውጭ አብያተ ክርስቲያናት ይገለገሉበታል ወይ?

4 የግራኝ መሐመድ ታሪክ የአበላሉ የሐያልነቱና የቁመቱ በአፈ ታሪክ እንደሚነገረው ነው ወይ?

ዲ ወንድሙ ባንተይዋሉ
ከደብረ ገሊላ አማኑኤል
አዲስ አበባ

• ዲያቆን ወንድሙ ስለጥያቄህና አስተያየትህ እናመሰግንሃለን ።

ዲሜጥሮስ የአጽዋማትና የበዓላት አወጣጥ የተወሰነ ባለመሆኑ ጌታችን ባረገ በ207 ዓመት በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት በዓቢይ በማዕከላዊና በንኡስ ቀመር ወስና የበዓላትንና የአጽዋማት አወጣጥ የዘመንን አቆጣጠር አወጣ ላልከው ጌታችን ባረገ በ180 ዓመት ነው እንጂ በ207 ዓመት አይደለም

2ኛ የዘመን አቆጣጠርም ከአበው ጀምሮ የነበረ ነው (ዘፍ.5፥3-6) የዘመን ሁሉ መለኪያና መቆጠሪያ የሆነው ንኡስ ቀመርም አብሮ የተመሠረተ ነው በሰፊው ምክንያቱን ሁሉ ለመረዳት ብትፈልገም ከመሥራት ይፈልቃል ዕቀት ከተባለው መጽሐፍ ውስጥ ክፍል 8ና ክፍል 9 ተመልከት 3ኛ/ የበዓላትና የአጽዋማት አወጣጥ በዘመነ አሪት የነበሩ አበው አጽዋማትንና በዓላትን በ29 ቀን ውስጥ ኢየዓርጉ ኢይወርዱ በሚል ውሳኔ ወስነው ሲሠሩበት የነበረ ነው ። በዚህ መሠረት ነው ዲሜጥሮስ ከመልአኩ ሊረዳ የቻለው የወሰነውም ውሳኔ የበዓላተ ሐዲስን ኢየዓርጉ ኢይወርዱ የሚለውን ነው ይህም 5 ጊዜ 7፥35 ቆጥሮ ደብረ ዘይት ሆሣዕና ትንሣኤ ጰራቅሊጦስ ከእሑድ አይውጣ የሚል ውሳኔ በዘመኑ የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉ በመስማማት ተቀብለው ሠርተውበታል ። ስለዚህ በዚህ መሠረታዊ ውሳኔ እኛ እንሠራበታለን ።

ከእኛ ጋራም መሠረቱን ይዘው የሚተባበሩን 1 ግብጽ 2ኛ ሶርያ 3ኛ አርመን 4ኛ ግሪክ ናቸው በኋላ ዘመን በበዓሉ አከባበር የተለዩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ ። ሆኖም ክርስቶስ አንድ ነው ክርስቶሳውያንም ሁላችን በአንድ መመሪያ መመራት ይገባናል ።

ስለ ሁለተኛው ጥያቄህ የኢትዮጵያ ምእመናን የትንሣኤን በዐል በየዓመቱ በኢየሩሳሌም ከውጭዎች ጋር ማለት ከምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን ጋር በአንድ ቀን ሲያከብሩ ከምዕራባውያን ጋር ግን በአንድ ቀን አያከብሩም ። ምክንያቱም እንደ ምሥራቃውያን አ ክርስቲያናት ሥርዓት ዐቢይ ጾም 50 ቀን ሲሆን እንደ ምዕራብ አ ክርስቲያናት 40 ቀን ብቻ ነውና ። በምሥራቃውያን ዘንድ ጾሙ 50 ቀን መሆኑ ከአርባ ቀን በኋላ ስለጌታችን ሕማማት በተለይ ለአንድ ሳምንት በጾምና በስግደት ቆይተው ትንሣኤን ስለሚያከብሩ ነው እርግጥ ኖሮ ኖሮ ሁሉም በአንድ ቀን ትንሣኤን የሚያከብሩበት ጊዜ አለ ።

በ3ኛ ቁጥር ባቀረብከው ጥያቄ እኛ ግእዝ ዕዝልና ራራይ እያልን እንደምንጠቀም ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አይጠቀሙም ። ምናልባት የዜማቸው ስልት በሙዚቃ ባለሞያዎች ቢመረመር ከ3 የዜማ ስልት ላይበልጥ ይችል ይሆናል ።

በመጨረሻ ስለ ግራኝ መሐመድ ስላቀረብከው ጥያቄ በአፈታሪክ እንደሚነገረው አይደለም ። ምንም ከሰው የተለየ አበላል አልነበረውም ። እርግጥ ጀግና ነበር እንጂ ከሰው ተፈጥሮ የተለየ ጉድ ፍጥረት እንዳልነበረ ስለ ግራኝ መሐመድ የተከታተሉት ጋርቺጋሎች ጽፈዋል ።

* *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ በፊት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንት ጋር ይሁን ። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ቁጥር 50 ላ “ወሶበ መልዐት ...” መረብዋ በመላች ጊዜ አወጡአት የሚለውን ንባብ አንድምታው ወንጌል ሲተረጉም ይህ ዓለም የሚያልፈው ጻድቃን ከነገደ ዲያብሎስ ልክ ሲሆኑ ነው ይላል ነገደ ዲብሎስ ከጻድቃን መብለጣቸውን ማን ያውቃል?

የመጽሔታችሁ ተከታታይ ቄስ ተመስገን ደምሴ ከሞጆ ከተማ

• ቄስ ተመስገን ደምሴ መጽሔታችንን እየተከታተሉ ተደጋጋሚ ጥያቄ በማቅረብዎ እናመሰግናለን ። ነገደ ዲያብሎስ ከጻድቃን መብለጣቸውን አይቶ የቆጠረ የለም ። እርግጥ አንዳንድ መጻሕፍት የዲያብሎስ ተከታዮች መላእክት እጅግ ብዙዎች መሆናቸውን ይገልጣሉ ። ታዲያ ጻድቃን እንደ ነገደ ዲያብሎስ ይበዙ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ለመግለጥ ሊቃውንት ተርጉመዋል ።



ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

እግዚአብሔር ነቢያትን ለምሳሌ አብርሃምና ሙሴን ሳሙኤልን ዳዊትን ሰሎሞንን ዮናስን ሲያነጋግር እንዴት ነው ? ተገልጾ ነው በራእይ ነው ቃል እየላከ ነው? ወይስ በመንፈስ ነው ? ይህ ስላልገባኝ አብራርታችሁ እንደምትገልፁልኝ እተማመናለሁ ።

ተማሪ ድባቤ መኮንን አዲስ አበባ

• ተማሪ ድባቤ፡- መጽሐፍ ቅዱስን በመከታተል ስላቀረብሽው ጥያቄ እናመሰግንሻለን እግዚአብሔር ቅዱሳን ነቢያትን ያነጋገረው ሀ/ በራእይና በሕልም) ዘኁል 12.6 ለ/በመልአክ (ዳን.9፥21) ነው ። በሌላም በተለያየ ሁኔታ አነጋግሮአቸዋል ።ለምሳሌ ዘጸአ 3.2-6 ነገሥት 19፥9-15 ተመልከቺ ። ይህም የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔርን ከቶ ሊያየው የሚችል ስለሌለ ነው ዘጸአ 33፥17-23 ። ነገር ግን በመጨረሻ በአንድ ልጁ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በግልጥ ተናግሮአል ዕብ. 1፥1-2 ።

* *

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ዐቢይ ጾምን ከጨረስን በኋላ እስከ ሰኔ ጾም ድረስ ረቡዕና ዐርብን ሳንለይ የቅባት ምግቦችን የምንመገብበት ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ ወይ?

ቄስ ገብረ ሚካኤል አበበ
ከሲዳሞ ቦዴቲ

• ከዐቢይ ጾም በኋላ እስከ ሰኔ ጾም ድረስ የቅባት ምግብ እንዳይበላ የሚያዘው ፍትሐ ነገሥቱ ነው አንቀጽ 15 ይመልከቱ ። እርግጥ በሐዋርያትም ትእዛዝ ይገኛል ። (ዲድስቅልያ)

## ጾመ ፍልሰታ ...

ከገጽ ፯ የዞረ

ጡት አስተያየት “በመሠረቱ በሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ድንግል ማርያም ፍልሰት (ዕርገት) ከነሐሴ 1-14 ቀን ጾም አለ ። ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደሚፈጸመው በየቀኑ ቅዳሴ የለም ። ሕዝናትም አይጾሙም ፣ ምን አልባት በጾሙ መካከል ቅዳሴ የሚቀደስበት ምክንያት ቢገኝ በጥዋት ይቀደሳል እንጂ እስከ ሰዓት አይዋልም ።



ሕንዳዊው ካህን ፋዘር ሻኪ

ከ14 የጾም ቀናት በኋላ በ15ኛው ቀን በዓለ ፍልሰትዋ ይከበራል ነሐሴ 15 ቀን ረቡዕ ወይም ዓርብ ቢሆን ስለ ክብረ በዓለ ፍልሰትዋ ጾም መሆኑ ቀርቶ ፋሲካ ሆኖ ይውላል ። ልደትና ጥምቀት በረቡዕና በዓርብ ቢውሉ እንደማይጾም ሁሉ በዓለ ፍልሰታም እንዲሁ ነው ። በ1947 ዓ.ም. የተገኘው የሕንድ የነፃነት በዓል ነሐሴ 15 ቀን ነው ። በአጋጣሚ በዓለ ፍልሰታ ከዚሁ የነፃነት በዓል ጋር በዕለት ስለተባበረ በሕንድ ብሔራዊ በዓል ሆኖ ይውላል” ብለዋል ።

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ ፍልሰት ከሕንድ የነፃነት በዓል ጋር በአጋጣሚ በዕለት በመተባበሩ በሕንድ ብሔራዊ በዓል ሆኖ ይውላል የሚለውን ዜና ስንሰማ ሌላም የሚታወሰን ነፃነት አለ ፣ ይኸውም “መሠረተ ሕይወት ማርያም ወጥንተ መድኀኒት ዘእምቀዲሙ ማርያም የሕይወት መሠረትና የደኅንነት ጥንት ናት” በማለት ኢትዮጵያዊው ደራሲ እንደ ተናገረው ድንግል ማርያም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለተገኘው መንፈሳዊ ነፃነትና ድኅነተ ነፍስ ምክንያት መሆንዋ ነው ። የደኅንነታችን ጥንት የመንፈሳዊ ነፃነታችን መሠረት የተገኘ በእርስዋ አማካይነት ነውና ።

ኢትዮጵያውያን ምእመናንም ጾመ ፍልሰታን ከሌሎች አጽዋማት ለየት ባለ ሁኔታ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ የሚጾሙትና በዓለ ፍልሰትዋን በታላቅ ሥነ ሥርዓት የሚያከብሩት በአማላጅነትዋ ደኅንነትን የምትሰጥ የፀጋ ፣ የፍቅርና የአደራ እናታቸው መሆንዋን በመተማመን ነው ።

ራደ አስረስ

== ። == ። ==

## ከቋጥኝ የተሠሩ...

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ዘዋውሮ ለመመልከት በተደረገው ጥረት 1ኛ ጓድ መኩንን ተሰማን የጉጂም ክፍለ ሀገር ባህል ሚ.ር.መ ቢ.ት ኃላፊን ና እንዲሁም ጓድ አምኃ አስረስንና ሌሎችን የመ/ቤቱን ባልደረቦች ከልብ እናመሰግናለን ።

ተስፋ ጥሩነህ



www.ethiopianorthodox.org

## ይህን ያውቁ ኖሯል ?


እጅጉ ረታ

በአርኪዎሎጂ አሰሳ ከመሬት ተቆፍረው ስለተገኙ የሸክላ ሰሌዳ መዛግብት ፤ በዚህ ዓምድ ሥር ጽሑፍ ማቅረቤ ይታወሳል ። ይህንንም መሠረት በማድረግ በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያው ምዕራፎች የተመለከተው የሥነ ፍጥረት ታሪክ ለሙሴ ከላይ ከአበው የተላለፈለት ቃል በቃል ፤ በትውፊት ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ ጽሑፍ አማካይነት መሆኑን ለማሳየት ሞክሬ አለሁ ። ዛሬ ደግሞ በአርኪዎሎጂ ምሑራን አካፋ ተቆፍረው ከወጡ የሸክላ ሰሌዳዎች ውስጥ ከጥፋት ውሃ በፊት የነበሩ እያን ዳንዳቸው የየዕለቱን ስነ ፍጥረት ታሪክ፡ እንደ ኦሪቱ መጽሐፍ አድርገው የሚያወሱ ሰባት የሸክላ ሰሌዳ ጽሑፎች በኤፍራጥስ ጨግሮስ ሸለቆ ተቆፍረው የመገኘታቸውን ዜና ለአንባቢያን አቀርባለሁ ።

እኒህም ሰሌዳዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ወይም ትምህርት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከሚያበቁ ተጨባጭ ማስረጃዎች እንደ ዓይነት ሆነው ሊቀርቡ የሚችሉ መሆናቸው አይጠረጠርም ። ይልቁንም በዚያን ሩቅ በነበረው ዘመን ሃሳብን በጽሑፍ መግለጽ ብቻ ሳይሆን በጽሑፍ የሠፈረውንም ሃሳብ በትክክል በስዕል መልክ ቁልጭ አድርጐ ማሳየት የተለመደ ተግባር መሆኑን ማወቁ ሳይጠቅም አይቀርም በሚል አስተሳሰብ የሚከተሉትን ሁለት በሸክላ ሰሌዳ የተቀረጹ ስዕሎች ፎቶግራፍ አቅርቤአለሁ ። ስዕሎቹም የፈተና ማሕተምና "አዳምና ሔዋን" በሚል ስም ይታወቃሉ ።

የስዕሎቹ ዝርዝር መግለጫ

(ሀ) የፈተና ማኅተም፡- በዚህ ክብ ማኅተም ላይ መሐል ለመሐል ፤ ፍሬ ያፈራ



የፈተና ማሕተም

የአንድ ዛፍ ስዕል ተቀርጿል ። በዛፉ በስተቀኝ የወንድ፤በስተግራ እጅዋን ወደዛፍፍሬ የዘረጋች የአንዲት ሴት ምስል ይታያል ። ከሴትየዋም በስተጀርባ አንድ እባብ በጭራው ቀጥ ብሎ ቆሞ ለሴትዮዋ በጆሮዋ አንዳች ነገር እንደሚነግራት ሆኖ ተስሏል ። ይህም ሔዋን በእባብ ምክር እንዴት እንደተሳሳተች በኦሪት ዘፍ ም. 3 ቁ1 - 8 ተጽፎ የምናነበውን ታሪክ የሚያስረዳ የስዕል መግለጫ መሆኑን አንባቢ በቀላሉ ሊገነዘብ እንደሚችል እሙን ነው ።

ስዕሉ የተገኘው በ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ላይ ሲሆን ፤ ዛሬ እንግሊዝ ሀገር በብሪቲሽ ቤተ መዘክር (ሙዝየም) በክብር ተቀምጧል ።

ለ ሁለተኛ ደግሞ "አዳምና ሔዋን" በሚል ስም የታወቀው ስዕል ነው ። ይህ ስዕል በ1932 ዓ.ም. ከነነዌ ፍራሽ ከተማ ሃያ ኪሎ ሜትር ርቃ ከምትገኝ ቴፔ - ጋዋራ ከምትባል ቦታ በአርኪዎሎጂስቱ ምሑር በዶክተር ኢ.ኤ. እስፓይዘር በሚመራው ቡድን ተቆፍሮ የተገኘ ነው ። ይህ ስዕል ከክርስቶስ ልደት በፊት 3500 ዓመት (ከጥፋት ውሃ በፊት ማለት ነው) ዕድሜ ያለው መሆኑን እኚሁ ዶክተር አረጋግጠዋል። ስዕሉ የተቀረጸው በድንጋይ ላይ ሲሆን፡ በስዕሉ ላይ እንደሚታየው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ራቁታቸውን ሆነው በሐዘን ተሸማቀውና አንገታቸውን ደፍተው እባብ እግር በእግር ተከትሏቸው በሐፍረት ሲራመዱ ይታያል ። የስዕሉ ቅርጽ ዛሬ በፔንሲልቫንያ ዩኒቨርሲቲ ሙዝየም (አሜሪካ) ይገኛል ።

ከእነዚህም በስተቀር በዚሁ ምድር ከጥፋት ውሃ በፊት ከነበሩት የከተማ



የአዳምና ሔዋን ማሕተም

ፍርስራሾች ውስጥ በዚያን ዘመን የነበረውን ኅብረተ ሰብ ኑሮ የሚያንፀባርቁ አያሌ ቁሳቁሶች ተቆፍረው ከመሬት ሊወጡ በቅተዋል ። አልፎ አልፎ ለመጠቃቀስም ያህል ከመዳብ ወይም ከነሐስ የተሠራ ጠገራ ፤ ማጭድ ፤ የአሳ መንጠቆ ፤ ለዓይነት (ለሞዴል) የተሠራ

ወደ ገጽ ፳፫ የዞረ



## በደብረ ታቦር ክብሩን አየን

ታቦር ከገሊላ ባሕር በምዕራባዊ ደቡብ በኩል 10 ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ ተራራ ነው ይህም ተራራ ከባሕር ጠለል 572ሜትር ከፍታ አለው"ባርቅ የተባለውጦረኛ ሕዝበ እስራኤልንይዞ በመዝመት ሲሳራ የተባለውን የሕዝብ ጠላት በታቦር ድል ነስቶ አሸንፏል" መሳፍንት ምዕ.4.ከቁ.6-14

መዝሙረኛው ዳዊት ታቦርና አርሞኤንም በስምህ ደስ ይላቸዋል ክንድህ ከኃይል ጋር ነው" ሲል በመዝሙር 88 በቁ. 12 ስለ ታቦር ተራራ ዘምሯል ይኸውም ታቦር የተባለው ተራራ በገሊላ ከሚገኙ ተራራዎች አንደኛው ሲሆን በዛብሎን ክፍል ውስጥ የሚገኝና ለሜራሪ ልጆች የተሰጠ ቦታ ነው ። 1ዜና 6:77

አዲስ ኪዳን ግን ረጅም ተራራ ከማለት በስተቀር ታቦር ብሎ ስሙን አይጠራውም ሆኖም ክርስቶስ በዚህ ተራራ ላይ ክብሩን እንደገለጠና የዚህም ተራራ ስም ታቦር መሆኑን ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ገልጠዋል ፤ የኢትዮጵያ ሊቅ ቅ/ያሬድም ይህንን ረጅም ተራራ ደብረ ታቦር እያለ በድጓው አስፋፍቶ ጽፏል

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ረጅም ተራራ የወጣው ብርሃነ መለኮቱን ክብሩንም ለመግለጽ ነው ። በዚህ ተራራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴና ከኤሊያስ ጋር ተነጋግሮአል እነዚህም ሁለት ታላላቅ ሰዎች በብሉይ ኪዳን ጊዜ ስለክርስቶስ ትንቢት የተናገሩ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ያስተማሩ ቅዱሳን ነቢያት ነበሩ ።

ከነቢያት መካከል ሁለቱ ቅዱሳን ነቢያት እንዲገኙ ያደረገውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቂሳሪያ ተገኝቶ "ደቀመዛሙርቱን ሰዎች እኔን ማ ይሉኛል? ሲል ጠየቃቸው ከእነሱም አንዳንዶቹ ኤልያስ አንዳንዶቹም ሙሴ ነው ይሉሃል አሉት እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ ቢላቸው አብዛኛዎቹ ኅብረተሰቡ ከሚለው ጋር ሲተባበሩ ጴጥሮስ ግን አንተ ክርስቶስ የህያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ሲል መሰከረ እየሱስም መልሶ ይህን በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ አለው" የማቴ ወንጌል ምዕራፍ 16 ከ13-18 ።

በዚህ አኳኋን ወደ ደብረ ታቦር ተራራ ጴጥሮስ ፣ ዮሐንስና ያዕቆብን ይዞ ወጥቶ ራሱ ኤልያስ ወይም ሙሴ አለመሆኑን ገለጠላቸው ከሞተ ብዙ ዘመን የሆነውንሙሴን ከመቃብር አስነስቶ ቀጥሎም በእሳት ሠረገላ ያረገውንና በተድላ ገነት የሚኖረውን ኤልያስን በተራራው እንዲገኝ አድርጐ አብረውት የነበሩት ደቀ መዛሙርት ሙሴ ነው ወይም ኤሊያስ ነው በማለት ሲጠራጠሩ እንዳይኖሩ ትምህርት ለመስጠት ነው ።

በማቴ ወንጌል በምዕራፍ 17 ቁ. 2 "በፊታቸው ተለወጠ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ" ይላል ። የክርስቶስ ፊቱ እንደ ፀሐይ የበራው የብርሃኑም ኃይል ያንፀባረቀው የብሉይ ኪዳን መሪ እንደነበረው እንደ ሙሴ ፊት ብርሃን አይደለም ይኸውም "ሙሴ ከሲና ተራራ ሲወርድ የፊቱ ቆዳ አንፀባረቀ አሮንና እሥራኤልም ይህንን ስላዩ ወደ እሱ ይቀርቡ ዘንድ ፈሩ ተሸፈንም እያሉ ጮሁ ሙሴም እግዚአብሔር ያዘዘውን ለእነሱ ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ በፊቱ መሸፈኛ አደረገ" ይላል ኦሪት ዘጸዓት ምዕ. 34.29-30 የሙሴ የጸጋ ነው የክርስቶስ ግን የባሕርይ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ከላይበጠቀስነ የማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 17 በቁ. 5 "ብሩህ ደመና ጋረዳቸው" ይላል ይህ በሲና እንደታየው ያለ አይደለም ። በሲና የታየው ደመና ጨለማ ነበር፤ በታቦር የታየው ግን ብሩህ ነበር። ከደብረሲና ደመና ውስጥ የቁጣና የፍርሃት ድምፅ ተሰምቷል ፤ ከደብረ ታቦር ደመና ግን "የምወደው ልጅ ይህ ነው" የሚል የፍቅር ድምፅ ተሰማ። በደብረሲና የተገለጠ የፍጡር የሙሴ ክብር ነበር ፤ በደብረ ታቦር ግን የሕያው ባሕርይ የክርስቶስ ክብር ተገልጦአል ።

የደብረ ታቦር በዓል በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው አከባበር

1ኛ ደብረታቦር ከዘጠኙ አበይት በዓላተ እግዚእ አንዱ ነው ስለዚህም ከዋዜማው ጀምሮ እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ ማህሌት ይቆማል ሊቁ ያሬድ ስለ በዓሉ የደረሰው መዝሙር ይዘመራል ይልቁንም «ስባሕኩከ በደብር በቅድመ ሙሴ ወኤልያስ ነቢያት ምእመናኒከ»በታማኞችህ ነቢያት በሙሴና በኤልያስ ፊት የባሕርይ ልጅነትህን መሰከርሁልህ የሚለው መዝሙር ለበዓሉ ልዩ ድምቀት ሰጥቶት ይውላል ።

2ኛ የደብረ ታቦር በዓል በቆሎ ተማሪዎች በኩል ያለው ይዞታ

የቆሎ ተማሪዎች በዓሉ አንድ ወር ሲቀረው በየመንደሩ ተዘዋውረው ጥሬ በልመና ይሰበስባሉ ከለመኑትም ጥሬ ግማሹን ጠላ ይጠምቃሉ ግማሹን ቆሎ ይቆሉታል በዚህ ሁኔታ ሲዘጋጁ ይሰነብቱና በደብረ ታቦር ዕለት የለመኑትን ኅብረተሰብ የደብሩን ካህናትና አለቃ አስተማሪዎቻቸውን ጠርተው ይጋብዛሉ በሚጋብዙበትም ወቅት እየዘመሩ ተጋባዡን ያስደስቱታል የደብረ ታቦር በዓል በቆሎ ተማሪዎች በኩል ይህን በመሰለ ይዞታ ሲከበር ኑሯል ።

3ኛ የደብረ ታቦር በዓል ከኅብረተሰቡ ጋር ያለው የባህል ግንኙነት

ግንኛውም ኅብረተሰብ በዋዜማውና በየዕለቱ ችቦ እያበራ ያከብረዋል ሴቶችም በዋዜማው እንደ ጥብኝ ወይም ሙልሙል አድርገው ከስንዴ ዱቄት የተቦካ ዳቦ በብዛት ይጋግራሉ የዕለቱ ዕለትም ወደ ቤት ሊጠይቅ ለሚመጣ ሰው ሁሉ ዳቦ ይቀርብለታል የተጋገረው ዳቦ ለየጐረቤቱ ይታደላል አንድ ሰው አምስት ወይም አሥር ልጅ ቢኖረው በልጆቹ ቁጥር ዳቦ ይወሰድለታል በጠቅላ

ወደ ገጽ ፲፯ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# የንግድ ቤት አይደለም’’

ለጸሎት የተለየ ቦታ እንዳለው ሁሉ ለንግድም የተለየ ስፍራ አለው ፤ በጸሎት ቦታ የንግድ ሥራ ፤ በንግድ ቦታ የጸሎት ተግባር ሊከናወን አይገባም ።

ለምሳሌ በንግድ ቦታ የተሠረቀው ፤ የተቀማው ፤ የሚንቀሳቀሰውና የማይንቀሳቀሰው ሊሸጥና ሊለወጥ ሲችል በጸሎት ቦታ ግን የእምነት ፤ የሰላም ፤ የፍቅርና የመሳሰሉትም መንፈሳውያን ተግባራት ይከናወናሉ እንጂ ከመንፈሳዊ ተግባር ውጭ የሆነ ሌላ ሥራ ሊከናወን ይችልም ።

የጸሎት ቤት የተባለችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ናት ቤተ ክርስቲያን ቤተ ንጽሕ ቤተ በረከት ስለሆነች ንጹሕ ያልሆነ ነገር ሁሉ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊገባ አይገባውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥና ውጭ የሚገለገልባቸው ዕቃዎች ሁሉ ንጹሐን እንዲሆኑ ያስፈልጋል ፤ ጸሎት ማለት ትርጉሙ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገሩት ሰዎች ፤ የሚነጋገሩበት የጸሎት ቦታ ከማንኛውም አስጸያፊ ተግባር ንጹሕ ሊሆን ይገባል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ ዓለሙን ለማዳን አንድ ሳምንት ሲቀረው በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ታላቅ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ በቤተ መቅደሱ አካባቢ ተደርድረው ሲሸጡና ሲለውጡ የነበሩትን ዕቃዎች ርግቦችና ወንበሮች ገለበጠና “ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፏል እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት” አላቸው ማቴ. 21 ፥ 13 ።

በቤተ መቅደሱ ከሚሸጡት ዕቃዎችና ርግቦች መካከል በሥርቆት በዝርፊያ የተሰበሰቡ ሲኖሩ ከሻጮችና ከለዋጮችም መካከል ወንበዴዎች ቀማፊዎች ይገኙ ነበር ። ቤተ መቅደሱ የጸሎት ቤት መሆን ሲታወቅ በቤተ መቅደሱ አጠገብ የነበረው ገበያ ለቤተ መቅደሱ ታላቅ ርኩሰት ነበር ይህ ሁኔታ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ በጣም ስላስቆጣው በቸልታ ሊያልፈው አልፈለገም ፤ የቤተ መቅደሱን የጽዳት ጉድለት ለማስወገድ ሲል የገመድ ጅራፍ አበጀና በዚያ ገመድ እየገረፈ የርግብ ሻጮችን ወንበራቸውን ገልብጦ ርግቦቻቸውን ከቤተ መቅደሱ ቅጽር አባረራቸው ክቡር ዳዊት ቀደም አድርጐ “ስለቤትህ የቀናሁት ቅንዓት አቃጠለኝ” ብሎ የተናገረው ቃል ፍጻሜን አገኘ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን በመሰለ መንገድ የጸሎት ቤት የሆነውን



በየቤተ ክርስቲያኑ በበዓላት ቀን የሚታየው ገበያ

ቤተ መቅደስ ከወንበዴዎች ከሌቦች አጽድቶታል ክርስቶስ ቤተ መቅደሱን ከቀማኞችና ከሌቦች ነፃ ካደረገ በኋላ በዚያው ቤተ መቅደስ ውስጥ በርከት ያሉ ድውያንን ፈውሷል ፤ ዕውራንን አብርቷል ፤ ለምጻሞችን አንጽቷል እንግዲህ በቤተ መቅደስ ፋንታ ቤተ ክርስቲያን ተከተለች በቤተ መቅደሱ ላይ ጉድለት አድርሰው በተባረሩት ነጋድያን ምሳሌዎች ሆነው የሚነገሩትም ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ጥግ በማድረግ ያልደከሙበትን ገንዘብ የሚቀሙና የሚሠርቁ ናቸው ።

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናትን ስንመለከት በቅጽራቸው ገቢ ውስጥ ሆነ ውጭ ጉመንና ድንች ፤ ሽንኩርት ፤ ሽንኩራ አገዳ ፤ ሲጃራ ፤ ጉዝጓዝ ፤ ቅመማ ቅመሞችንና የመሳሰሉትም ሲቸረቸሩ እናያለን በምን ጽሑፍም በኩል የተመለከትን እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ያልሆኑና የቤተ ክርስቲያንን ህልውና የሚቃወሙ ጽሑፎች በየአብያተ ክርስቲያናቱ ቅጽረ ገቢ ሲሸጡ ይታያሉ ፤ በመሠረቱ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለመጸለይ የሚመጡት ምዕመናን ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ሊገዙት የሚገባቸው ንዋያተ ቅድሳትንና መንፈሳውያን ጽሑፎችን ሲሆን የማይፈልጓቸውን ዕቃዎችና ጽሑፎች ያለ ፈቃዳቸው ገዝተው ይዘው ወደቤታቸው ይመለሳሉ ፤ ለምእመናን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚሸጡት ዕቃዎችና ጽሑፎች ሁሉ ለምእመናን የቤተ ክርስቲያን ንዋያት ስለሚመስሏቸው ቤተ ክርስቲያንን በምክንያት የረዳን እየመሰላቸው ለገንዘባቸው ሳይሰስቱ ዕቃዎችን ይገዛሉ ።

የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ግን ይህንን የተገነዘቡት አይመስሉም ፤ ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሊሸጡ የማይገባቸው ዕቃዎችና ጽሑፎች እንዲሁም ቅመማ ቅመሞች ዶሮዎችና የመሳሰሉትም ሲሸጡና ሲለወጡ ዝም ብለው ይመለከታሉ ፤ እንደዚህ ያለውን ተግባር በቸልታ የሚመለከቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች የክርስቶስን አርያና ምሳሌ ለመከተል ፍላጐት የሌላቸው ፤ ስለቤተክርስቲያንም ልማትና ዕድገት የማያስቡ ናቸውና ወደፊት ሊያስቡበት ይገባል ።

በቤተ ክርስቲያን አካባቢ መሸጥና መለወጥ ያለባቸው የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳትና መንፈሳውያን ጽሑፎች ፤ መንፈሳውያን ካርዶች ናቸው እነርሱም ቢሆኑ ብዙ ትርፍ በሚያጋብሱ ነጋዴያን እጅ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እጅ ተሸጠው ተመልሰው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዋል ይገባቸዋል ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሥነ ጽሑፎች ፤ ስዕሎች ፤ ካርዶችና የመሳሰሉትም እንኳን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቅድስትና በቆመ ብእሲው እንዲሁም በቅኔ ማኅሌት ቢሸጡ ጸያፍ አይመስለንም ።

የውጭ ሀገር አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳውያን ጽሑፎችን ፤ ሥዕሎችን፤ መስቀሎችን ፤ ሻማዎችን ፤ መጽሔቶችን ፤ ካርዶችን የሚሸጡት በቤተ ክርስቲያን ገቢ ውስጥ ነው ፤ ይህንንም የሚያደርጉት ገቢው ተመልሶ ለዚያው ቤተ ክርስቲያን በመሆኑና ምእመናንም በቀላል ዋጋ መንፈሳውያን ጽሑፎችን እንዲያገኙ ነው ። በእኛም ቤተ ክርስቲያን ቢሆን እንደዚህ ያለው መንፈሳዊ ተግባር ቢፈጸም እንደ ስህተት ሲቆጠር አይገባውም እንላለን ቤ/ክርስቲያናችን ባሁኑ ጊዜ የምታሳትማቸው መንፈሳውያን ጋዜጦችና መጽሔቶች አሏት ፤ እነርሱም የሚታተሙት በከፍተኛ ወጭ ሲሆን የሚሸጡት ግን እጅግ በጣም አነስተኛ በሆነ ዋጋ ነው ፤ ይህም የሚሆነው የቤተ ክርስቲያን ዓላማ በጽሑፎች ትርፍ ለማግኘት ሳይሆን ምዕመናን መጽሔቶችንና ጋዜጦችን በማንበብ እንዲጠቀሙ ነው ።

የቤተ ክርስቲያንንም ሥነ ጽሑፎች ለመሸጥ የሚቻለው በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለሚገኙ ምዕመናን ስለሆነ በየዓመት በዓሉ ፤ በየወር በዓሉ ፤ እንዲሁም በዕለተ ሰንበት በየሳምንቱ መሸጥ አለባቸው የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ያልገባቸው አንዳንድ ሰዎች ግን ጉዳዩን ባለማጣራት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምእመናን መሸጥ የሚገባቸውን ጽሑፎች እንዳይሸጡ ሲከላከሉ ይታያሉ ።

በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚቸረቸሩትን ቅመማቅመሞች ግን እየተመለከቱ ዝም ይሏቸዋል ፤ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የማይገባ ሥራ ሲሠራና ጉድለት ሲደርስ እየተመለከቱ በቸልታ ማለፍ ተገቢ አይመስለንም ክርስቲያኖች ሁሉ መከተል ያለባቸው የክርስቶስን አርአያ ነው ፤ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ ላይ የደረሰውን ጉድለት በቸልታ አልተመለከተውም ቤተ መቅደሱን ጥግና መከታ አድርገው እየቀሙና እየሠረቁ እያመጡ የሚሸጡትንና የሚለውጡትን ሰዎች ከነንዝቻቸው ከቤተ መቅደሱ ገቢ እንዳስወጣቸው አሁንም ቤተ ክርስቲያንን ጥግ በማድረግ የግል ጥቅማቸውን ለማዳበር የሚሸጡትንና የሚለውጡትን ከቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ገቢ የሚያስወግድ እውነተኛ አስተማሪ ያስፈልጋል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ቤቴ የጸሎት ቤት እንጂ የንግድ ቤት አይደለም” ብሎ በተናገረው ቃል መሠረት ቤተ ክርስቲያን ከአልጠግብ ባዮች ከችርቻሮ ንግድ መጽዳት አለባት ።

ቤተ ክርስቲያን የጸሎት የስጊድ የምጽዋትና የመሳሰሉትም መንፈሳውያን ምግባራት መፈጸሚያ ስለሆነች እርሷን ምክንያት አድርገው የሚሠርቁ የሚቀሙ ያለአግባብ የሚነግዱና የመሳሰሉትንም ሥጋውያን ተግባራት የሚያከናውኑ ሁሉ ከዚህ መጥፎ ተግባራቸው መገታት እንደሚገባቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መልእክቷን ታስተላልፋለች ።

ይህንን የማይገባ ሥራ ለማስወገድ ካህናትና ምእመናን የመተባበር መንፈሳዊ ግዴታ አለባቸው የጸሎት ቤት የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የቀማኞች ዋሻ የሌቦች መሸሻ የሸቀጣ ሸቀጦች መቸርቸሪያ የጥቅም ማጋበሻ ልትሆን አይገባምና ።

ቄ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ

---

## በደብረ ታቦር ...

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ላው ዘመድና ዘመድ ዳቦ እየተያዘ የሚጠያየቅበት የተነፋፈቀ ሁሉ የሚገናኝበት የተራራቀ ሁሉ የሚቀራረብበት በዓል በመሆኑ በዓሉ በኅብረተሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ ተወዳጅነት አለው ስለዚህ እስከ3 ቀን ድረስ የዳቦ መለዋወጥ ይቀጥላል ይህም የሚያሳየን ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ለሰላምና ለፍቅር እንደመጣ ነው ።

4ኛ የደብረ ታቦር በዓል በልጆች በኩል ያለው ልማድ

ወንዶች ልጆች ከዋዜማው ጀምሮ በቡድን በቡድን እየተከፋፈሉ ዳቦና ገንዘብ የሚቀበል ልጅ ከመካከላቸው ይመርጣሉ ከዚህ በኋላ በየመንደሩ እየዞሩ የባህል ዘፈን እየዘፈኑና የሰዉዎችንም ስም እያወደሱ ዳቦና ገንዘብ ይቀበላሉ በዕለቱ እየጨፈሩ ካረፈዱ በኋላ ጨፍረው ያገኙትን ዳቦ አንድነት ተሰብስበው ይመገባሉ ገንዘቡንም ተከፋፍለው ለየችግራቸው ያውሉታል ።

ስለዚህ በልጆች በኩል የቡሄ ወይንም የደብረ ታቦር በዓል የተወደደና በጣም የሚናፈቅ ነው እንግዲህ የደብረ ታቦር በዓል በኅብረተሰቡና በልጆቹ በኩል የሚታወቀው ቡሄ በሚል ስም ነው አባቶች ቡሄ ማለት በራ ፤ ብርሃን ማለት ነው ስለሚሉ በደብረ ታቦር የበራውን ብርሃን ያመለክታናል ።

እሰቶ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ





www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅርጸ ቅርጽ ፣ በሥነ ጽሑፍና በታሪካውያን ቅርሶች የታወቀች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት ፤ እነዚህንም ጥንታውያንና ታሪካውያን ቅርሶች በሚገባ ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ይቻል ዘንድ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር የንዋየ ቅዱሳትና ቅርሳ ቅርስ አጠባበቅ መምሪያ ከተቋቋመ ዓመታት አልፈዋል ።

መምሪያው እስከአሁን ድረስ በጥናት ላይ ስለነበር ምንም እንኳን ብዙ የሥራ ፍሬ ባያሳይም ፣ ለወደፊቱ ግን ተጨባጭነት ያለው የሥራ ውጤት ለማሳየት የሚከተለውን ፕላን አዘጋጅቶአል ። ይህም ፕላን አሁኑኑ በሥራ ተተርጉሞ አጥጋቢ ውጤት እንደሚያስገኝ በተስፋ ይጠበቃል ።

## ፕላን

የእናት ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አርኪዮሎጂና ቅርሳቅርስ የብራና መጻሕፍት ብሔራዊ ሙዜም

### ክፍል 1

ሀ. የጥንት የብራና መጻሕፍት ጥበቃ ዋና ክፍል ፤

1. የብራና መፋቅና ማደራጃ ክፍል
2. በጥንት የኢትዮጵያ ሥራ የሰባት ዓይነት ቀለም ቅመማ ሥራ
3. ያረጁ የጥንት መጻሕፍት በነበሩት መልክ እንደገና መጻፍ
4. በተለያዩ ዓይነት ቀለም ቆዳ መንከርና የመጻሕፍት ድጉሳ ሥራ

### ክፍል 2

ለ. ከጥንት አባቶቻችን ሲያያዝ የመጣ የኢትዮጵያውያን ዓይነት ሥዕል ዋና ክፍል ፤

1. ቅድመ አክሱማይ የሥዕል ሥራ
2. አክሱማይት ዓይነት የሥዕል ሥራ
3. ድኅረ አክሱማይት ዓይነት የሥዕል ሥራ
4. በብሉይ ኪዳን እምነት ውስጥ በኢትዮጵያ የሥዕል ዓይነት
5. የክርስትና እምነት ከተጀመረበት ዘመን አንስቶ ያለው የሥዕል ዓይ ዓይነት

### ክፍል 3

ሐ. የባሕልና የታሪክ ቅርሳቅርሶችን እንደነበሩ አስመስሎና አሻሽሎ የሚሠራ የጥገና ዋና ክፍል ፤

1. ከተፈጥሮ ዕውቀት ጋር የዓርትና የሥዕል በቂ የሆነ ችሎታ ያላቸው ሰዓሊዎች
2. ሥዕሉን ወደ ታሪክ የሚለውጡ
3. ታሪኩን ወደ ሥዕል ለውጠው የሚሠሩ
4. የጥንቱን ቅርጸቅርጽና የሕንፃ ሥራ እንዳለ የሚጠግኑና አስመስለው የሚሠሩ
5. በጥንቱ ዓይነት ቁም ጽሑፍና የተለያየ
6. የሐረግ ጥበብ የሚያውቁ

### ክፍል 4

መ. የጥንት ቅርሳቅርሶች አጠባበቅ ብሔራዊ ሙዜም ዋና ክፍል ፤

1. በሕዝብ የሚጐበኙ የተለያዩ የጥንት ቅርሳቅርስ ክፍል ፤
2. ለሕዝብ የሚታይ የጥንት ክታብ መልክ አሮጌ መጻሕፍት ክፍል
3. የሚጐበኙና የሚነበቡ የብራና መጻሕፍት ክፍል
4. ለሕዝብ የሚታይ የተለያዩ የጥንት ሥዕሎች ክፍል
5. ለሕዝብ የሚታይ የተለያዩ መስቀሎች ክፍል
6. የጥንቱን መጻሕፍት በዘመናዊ ኢትዮጵያዊ የሚያዘጋጅ የትርጉም ክፍል

### ክፍል 5


ሠ. ቅርሶቹን በዘመናዊ ሁኔታ እያዘጋጀ ለሕዝብ የሚያቀርብ የሕትመት ዋና ክፍል ፤

1. ዘመናዊ የሆነ የመጻሕፍትና የተለያዩ ካርዶች ማተሚያ
2. የጥንቱን መጻሕፍት በዘመናዊ ኢትዮጵያዊ የሚያዘጋጅ የትርጉም ክፍል
3. በክታብ መልክ የተጻፉ የብራና መጻሕፍት የሚያሣትም
4. በእጅ የተጻፉ የብራና መጻሕፍት እያሳተመ ለሕዝብ የሚያቀርብ
5. የብራና መጻሕፍቱን ለትውልድ ለማስተላለፍ ማይክሮ ፊልም የሚያነሳ

### ክፍል 6

ረ. የማስታወቂያና የመገናኛ የገቢ ምንጭ ዋና ክፍል

1. በካርድ የታተሙ የተለያዩ የሥዕል ዓይነቶችን ለሕዝብ የሚያስተዋውቅ
2. የመስቀል ዓይነቶችን በተለያዩ ካርድ እየቀረጸ ለሽያጭ የሚያቀርብ
3. በተለያየ ሥዕልና ሐረጐች የብራና መጻሕፍትን በካርድ የሚያስቀርጽ
4. የታተሙ መጻሕፍትና የተለያዩ በካርድ የተቀረጹ ቅርሳቅርስ መሸጫ ክፍል



አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ የንዋየ ቅድስት የብራና መጻሕፍት ቅርሳቅርስ ጥናትና ዕቅድ መምሪያ ኃላፊ



# የጤና ዐምድ

## የአስም በሽታ

አዘጋጅ ጥላሁን ተካ

አስም በማንኛውም ዕድሜ የሚገኝ ከዓለም ውስጥ ከ1-2 በመቶ (1% - 2%) የሚሆኑትን ሕዝቦች የሚያጠቃ በሽታ ነው ። ሆኖም ግማሽ የሚሆኑትን በሽተኞች ዕድሜአቸው 10 ዓመት ከመድረሱ በፊት ሲለክፋቸው ሌሎች 1 3ኛ የሚሆኑትን ደግሞ 40 ዓመት ሳይሞላቸው በፊት ይይዛቸዋል ። በአዲስ አበባ ውስጥ በአንድ ሆስፒታል በተደረገው ጥናት 2.7 በመቶ (2.7%) የሚሆኑት በሽተኞች በአስም ምክንያት ወደ ሆስፒታል እንደሚገቡ ተረጋግጧል ።

### አስም ምንድነው ?

በአጭር አነጋገር አስም በሳምባ ውስጥ የሚገኙ ትናንሽ የአየር ማስተላለፊያ ቧምቧዎች የመጥበብ ውጤት ነው ። ይህም በነርቭ ወይም አለርጂን አማካይነት

1 ትናንሽ የዓየር ማስተላለፊያ ቧምቧዎች የጡንቻ ግድግዳዎች ሲኮማተሩ

2 በተጨማሪም የግድግዳዎቹ የውስጠኛው ክፍል ወይም ሽፋን (ሙከዛ) ሲያብጥ)

3 ወፍራምና የሚዝለገለጉ ፈሳሾች ያለቅጥ ቧምቧዎቹን ሲሞሉት ነው።

በእነዚህ ለውጦች የተነሳ የአየር ማስተላለፊያ ቧምቧዎቹን በድንገት ይጠባሉ ። ወዲያው ደግሞ ወደቀድሞው መጠናቸው ይመለሳሉ ። ሆኖም እንደበሽታው የዕድሜ ዘመን መጨመር በአንዳንዶች ላይ የአየር ማስተላለፊያ ቧምቧዎቹ እየጠበቡ ከመሄዳቸውም በላይ ወደ ቀድሞ መጠናቸው ፈጽሞ አይመለሱም ። እንግዲህ አስም ድንገት የሚያፍንና ትንፋሽ የሚያሳጣ በሽታ ሲሆን በጠቅላላው አስም ባለበት ሰው ላይ ሦስት ዋና ዋና ምልክቶች ይከሠታሉ ። እነርሱም ሳል ፤ ትንፋሽ ማጠርና ማንኳረፍ ናቸው ።

### መነሻውስ ?

የአስም መነሻው በትክክል ተለይቶ ባይታወቅም ፤ በአብዛኞቹ በሽተኞች ላይ የሚከተሉት ሁኔታዎች ለመነሻው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው ።

1. ከዘር ወደዘር የሚተላለፍ መሆኑ

2. በአንዳንድ ነገሮች (አለርጂን) የተነሳ መቀስቀሱ እነዚህም የአበባ ዱቄት ፤ የእንስሳ ቆዳና ፀጉር ፤ የቤት አቡዋራ ሲሆኑ ከምግብ ደግሞ እንቁላል ፤ ወተት ፤ ዓሣ የመሳሰሉት ከመድሃኒት ደግሞ አስፒሪን ፤ ፔኒሲሊን ፣ ኢንዶሜታሲን የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

3. ሳይታሰብ በሚፈጸም የነርቭ ሥራ ምክንያት

ድንገት ለብርድ መጋለጥ ፤ ከባድ ሥራ መሥራት ፤ በኃይል መሳቅ ፤ ከበድ ያለ ምግብ መብላትና የመሳሰሉት አስምን ይቀሰቅሳሉ ።

4. በአእምሮ መታወክ የተነሳ

ጭንቀት ፤ ፍርሃት ፤ በኑሮ በሕይወት የሚደርስ ውጥረት ሰላም በማጣት

5. በአየር ማስተላለፊያ ቧምቧዎችና በሳምባ ላይ በሚደርሱ ጉዳቶች የተነሳ ለምሳሌ ጉንፋን ፤ የሳምባ ምች የመሳሰሉት አስምን ይቀሰቅሳሉ ።

### ሕክምናው

1ኛ/ እላይ ከተራ ቁጥር 2 -5 ያሉትን ሁኔታዎች አጥብቆ መከላከል

2ኛ/ በየጊዜው ስለበሽታው ሐኪም ማማከር ። ሐኪሙም እንደበሽታውና እንደሁኔታው የተለያዩ መድኃኒቶችን ሊያዝዝ ይችላል ። በአንዳንድ አገሮች ምንም እንኳ አስቸጋሪ ቢሆንም በሽተኛውን ለአስም ያበቁትን ነገሮች (አለርጂን) በማወቅ በኩል በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ጥናትና ክትትል በመደረግ ላይ ነው ። እነዚህም አለርጂኖች ከታወቁ ትንሽ በትንሹ በመውጋትና በሽተኛውን በማለማመድ ሥራቸውን ለማርከስ እየተሞከረ ነው ።

3ኛ/ ወደ ሆስፒታል ማስገባት ፤ እነዚህም በሚሰጣቸው መድኃኒት ምንም ያልተረዱ ከዕለት ወደ ዕለት ሳሉም ሆነ ማፈኑ በይበልጥ ያስቸገራቸውንና እስታቱስ አስማቲኩስ የተባለውን የአስም ክፍል የያዛቸውን ያጠቃልላሉ ።

### እስታቱስ አስማቲኩስ ምንድነው ?

ይህ በጣም አደገኛው የአስም ክፍል ነው ። አስሙ በድንገት ይጀምረዋል ። በሽተኛው ያስለዋል ፤ ያንኳርፋል ደረቱን ያስጨንቀዋል ፤ የአየር ረሀብ ይታይበታል ። ቀድሞ የሚወስደውን መድኃኒት ወስዶ ምንም አልረዳውም ማፈኑ እየደጋገመ ይቀጥላል ። ከሰዓታት በማለፍ ከአንድ ቀን በላይ ድረስ ያስቸግረዋል ። ያልበዋል በጣም ያስጨንቀዋል ጣር ይበዛበታል ። ይህንና ይህን የመሳሰሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በሽተኛውን ቶሎ ወደ ሆስፒታል መውሰድ ያስፈልጋል ።

### ወደፊትስ

የአስም በሽታ የያዛቸው ሕፃናት ለአካለ መጠን ሲደርሱ በሽታው እየቀነሰ በመጨረሻም እየጠፋ ይሄዳል ። 50 በመቶ (50%) የሚሆኑት ሕፃናት ሙሉ አዋቂ ሰው ሲሆኑ በሽታው ፈጽሞ ይለቃቸዋል ። በመካከለኛ ዕድሜ ላይ አስም የያዛቸው ሰዎች በሽታው ከመራዘሙ በስተቀር ሕክምናቸውን በደንብ ከተከታተሉ ፤ ከቻሉም አካባቢያቸውንና የዕለት ኑሮአቸውን ከለወጡ ከ75 በመቶ (75%) በላይ የሚሆኑትን ምንም ዓይነት ከባድ ጉዳት አይደርስባቸውም የአእምሮ መታወክንና በዓየር ማስተላለፊያ ቧምቧዎች እንዲሁም በሳምባ ላይ የሚደርሱትን ጉዳቶች ከተከላከሉ አልፎ አልፎ የማፈን ሁኔታ ከመፈጠሩ በስተቀር እንደማንኛውም ሰው መልካም ኑሮአቸውን ሊመሩ ይችላሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የምእመናን ድምፅ



ይህ አምድ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር ተሐድሶ የምትራመ ድበትና የምትሻሻልበት ክርስቲያኖች ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው በቀና መንፈስ አስተያየት የሚያቀርቡበት ነው ፡፡በዚህ ዓምድ ሊቀርቡ የሚገባቸው ጽሑፎች የቤተ ክርስቲያናችን ውሳኔዎች ሳይሆኑ የግለሰቦች አስተያየት መሆናቸውን

ተከታታዮች በቅድሚያ እንዲያውቁልን እንፈልጋለን ፡፡

አዘጋጅ ነቶኝ ጥበብ ወንድም የስልክ ቁጥር 11-66-16 የመልእክት ሣ.ቁ. 3137 አዲስ አበባ

ባለፉት ተከታታይ መጽሔቶቻችን የመቃብር ቦታ ችግርና አንዳንድ አለ መግባባት ያለባቸውን አብያተ ክርስቲያናትና የመቃብር ቦታ ያላቸውን አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ጠይቀን ያገኘነውን በዚሁ በምዕመናን ድምፅ ማቅረባችን ይታወሳል ፡፡

በዛሬውም ዝግጅታችን የመቃብር ቦታ የሌላቸውን የጉላ ቅዱስ ሚካኤልን አስተዳዳሪ ጠይቀን ያገኘነ ውን መልስ አቅርበንላችኋል ፡፡

<u>ጥያቄ</u>፡— መልአከ ብርሃን ናሁ ሠናይ ወርቅነህ ባለፈው የምዕመናን ድምፅ ዝግጅታችን ከደብረ አሚን ተክለሃይማኖት አስተዳዳር ስለመቃብር ቦታ ጠይቀናቸው የሰጡን መልስ ከጉላ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳርና ከራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጋር ለመወያየት ደብዳቤ ተጽጽፈን ነበር ግን ልንገናኝና ልንወያይ አልቻልንም ብለዋል ተወያይታችሁ መፍትሔ ለመስጠት ያልፈለጋችሁት በመቃብር ቦታ በኩል ችግር የለባችሁም ማለት ነው?

<u>መልስ</u>፡- ለመቃብር ቦታ በጣም ከፍ ያለ ችግር አለብን ከደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት አስተዳደር ጋራ ተወያይተን መፍትሔ ለመስጠት ያልቻልን በት ግን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የመቃብር ቦታ የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዙዎቹ በመሆናቸው ቤተ ክህነቱ ለሁሉም መፍትሔ ይፈልግላቸው ይሆናል በማለት ነው ፡፡

<u>ጥያቄ</u>፡- ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያን ብዙ አገልግሎት ይፈልጋሉ በአንዳንድ ቦታ ካህናት በአገልግሎት በኩል እምብዛም ሊያረኩ አለመቻላቸው ይነገራል ይህ በእናንተ ቤተ ክርስቲያን በኩል ምን ያህል ተሟልቷል?

<u>መልስ</u>፡- ለምዕመናኑ የጉላ ሚካኤል ካህናት ቦታ በማዘጋጀት መቋሚያ ጠበል በመስጠት የሚያሳዩት መልካም ጠባይና ትህትና ምዕመናን ካሰቡት በላይ ስለሆነ በካህናት ላይ የሚያሰሙት ምንም ቅሬታ የለም ፡፡

<u>ጥያቄ</u>፡- ምዕመናንን በሰበካ ጉባኤው ደንብ ወክለው የሚሠሩ መመረጣቸው ግልጽ ነው በአሁን ጊዜ በአንዳንድ ቦታ ካህናትና ምዕመናን በአለመስማማት ቅሬታ እየፈጠሩ የቤተ ክህነትን ቢሮ እያጣበቡ አስቸግረዋል ይባላል በእናንተ በኩልስ ይህ አይነት ቅሬታ አለ ወይ?

<u>መልስ</u>፡- የጉላ ሚካኤል የሰበካ ጉባኤና በካህናት በኩል የቤተ ክህነቱን ቢሮ እስከ ማጣበብ የደረሰ ምንም ቅሬታ የለም ፡፡

<u>ጥያቄ</u>፡- አንዳንድ የሰበካ ጉባኤ አባላት የአስተዳደር በደል አድርሰው በቤተ ክህነት ክስ ሲመሠረትባቸው ቤተ ክህነት ምን አገባው የሚሉ አንዳንድ የሰበካ ጉባኤ አባላት እንደ አሉ ይነገራል ይህንንስ እንዴምን ይመለከቱታል?

<u>መልስ</u>፡- የጉላ ሚካኤል የሰበካ ጉባኤ አባላት የቤተ ክህነቱን መብት ጠብቀው ከመሥራት በቀር ከቤተ ክህነት ውጭ ነን የሚለው ሥነ ሥርዓት የለሽ አቋም በሐሣባቸውም የለም ፡፡

<u>ጥያቄ</u>፡- ለማጠቃለል ያህል ወደተነሣንበት ዓላማ መለስ እንበልና ስለ መቃብር ቦታ ችግር ከላይ መግለጻችን ይታወሳል ለወደፊት ችግር እንዳይፈጠር በእናንተ በኩል ምን ዓይነት ዕቅድ አላችሁ?

<u>መልስ</u>፡- ስለ መቃብር ቦታ እጦት ግን ከላይ እንደጠቀስነው ጠቅላይ ቤተ ክህነት አስቦ መፍትሔ ካልፈለገለት በኛ በኩል ያለን እቅድ የመቃብር ቦታ ከሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ክፍት ቦታ ከመንግሥት ጠይቀን ለማስከለል በማስተባበር ላይ ነን ፡፡



# ሊቃውንቶቻችን

**መምህር ደስታ ጎሹ (1860-1931 ዓ.ም)**

መምህር ደስታ ጎሹ በጎጃም ክ ሀገር በሞጣ አውራጃ በአሸመን ወረዳ በ1860 ዓ.ም. ተወለዱ ፡፡

መምህር ደስታ ፡- ከንባብ እስከ ጸዋትወ ዜማ መሪጌታ ሐዲስ ከተባሉ መምህር ተማሩ ፡፡ በዘጠኝ ዓመታቸው ቅኔ እንደ ተቀኙ ፣ ቅኔም በተቀኙ ጊዜ ልጅ ከመሆናቸው የተነሣ በነጋሪት ላይ ቆመው ይቀኙ እንደነበር ይነገርላቸዋል፡፡ መምህር ደስታ በዜማ በቅኔና በሥልጣነ ክህነት ቤ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በ18 ዓመታቸው ወደ ትርጓሜ መጻሕፍት ት ቤት ገብተዋል ፡፡ የአስተማሩአቸው ሊቃውንትም 1ኛ ሊቅ አካለ ወልድ በቦሩ ሥላሴ ወሎ 2ኛ ሊቅ ወልደ ሚካኤል በዜና ማቆስ ገዳም ሸዋ ፣ 3ኛ መሪጌታ ኪዳኑ ናቸው ፡፡ ከእነዚህ ሦስት ሊቃውንት የብሉያትንና የሐዲሳትን ትርጓሜ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ፡፡ በዚህም ሙያቸው ከኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደ አንዱ ተቆጥረዋል ፡፡

ጠዋል ፡፡ ከአምስቱም አንዱ መምህር

**የትምህርት ጉባኤያቸውና ደቀ መዛሙርቶቻቸው**

መምህር ደስታ በመምህርነት ከተመረቁ በኋላ ጉባኤ ዘርግተው ትርጓሜ መጻሕፍትን ማስተማር ጀምረዋል ፡፡ ደቀመዛሙርቶ ቻቸውም በጣም ብዙዎች ነበሩ ፡፡ ከብዙዎቹም መካከል 1ኛ መምህር ገሪማ በኋላ አቡነ ሚካኤል ጳጳስ ዘጐንደር ፣ 2ኛ መ ሰይፈ ሥላሴ የመንበረ መንግሥት ገብርኤል አስተዳዳሪ የነበሩት 3ኛ ንቡረ እድ ገ መስቀል በኋላ አቡነ ዮሐንስ ጳጳስ ዘትግራይ 4ኛ አለቃ ፋንታዬ ፣ 5ኛ መምህር ፊላታዎስ ፣ 6ኛ አለቃ እምሖ ፣ 7ኛ ሊቀ ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ይገኙባቸዋል ፡፡

**በአስተዳዳሪነት የተዘዋወሩባቸው ገዳማትና አድባራት**

መምህር ደስታ በማስተማርና በማስተዳደር ቤተ ክርስቲያንን በትጋት አገልገለዋል፡፡ በአስተዳዳሪነት ያገለገሉባቸው ገዳማትና አድባራትም የሚከተሉት ናቸው፡-1ኛ ዋሮ ኪዳነ ምሕረት ወሎ 2ኛ የሰባ ማርያም ወሎ ፡፡ 3ኛ ገረገራ ጊዮርጊስ ወሎ 4ኛ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ወሎ ፣ 5ኛ አንኮበር ሚካኤል ሸዋ ፣ 6ኛ ፍርኩታ ኪዳነ ምሕረት ሸዋ ፣ 7ኛ መንበረ መንግሥት ገብርኤል አዲስ አበባ ናቸው ፡፡ ከዚህም ሌላ ራስ ወሌ በሚያስተዳድሩት አገር ሁሉ ሊቀ ካህናት ሆነው አስተዳድረዋል በዚህም ጊዜ ሁሉ ጉባኤያቸው አልታጠፈም ነበር በመንበረ መንግሥት ገብርኤል በነበሩ ጊዜ ለንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ ትርጓሜ የሚያሰሙ እርሳቸው ነበሩ ፡፡

**<u>ጵጵስና</u>**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ. ክርስቲያን ከራስዋ መነኮሳት መካከል ጳጳሳትን እንድትመርጥ ከእስክንድርያ ቤ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ጋር ስፊ ክርክር ተደርጎ ወደ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ 1921 ዓ.ም. 5 ጳጳሳት ተመርጠዋል ፣ ካምስቱም አንዱ መምህር ደስታ ነበሩ ፡፡ እርሳቸውም ብፁዕ አብርሃም ተብለው የጐንደርና የጐጃም ጳጳስ ሆነዋል ፡፡

**<u>ሊቀ ጵጵስና</u>**

ጠላት ወደ ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ ከእስክንድርያ ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ በኢትዮጵያ የነበሩት ሊቀ ጳጳስ ቄርሎስም ሸሽተው ወደ ሀገራቸው ሄዱ በዚያ ጊዜ አቡነ አብርሃም ኅዳር 17 ቀን 1930 ዓ.ም. በኢትዮጲያ ሊቃውንት ካህናትና ምእመናን ተመርጠው ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም. የሊቀ ጵጵስ ስናውን ሥልጣን ተረክበዋል ፡፡

ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አብርሃም በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ሳሉ ደቀ መዛሙርትማስተማራቸውንና የማኅሌት አገልግሎታቸውን አላቋረጡም ነበር ፡፡ ለምሳሌ አንድ ጊዜ ከጠላት ወረራ በፊት በጐንደር ሀገረ ስብከታቸው ሐምሌ 19 ቀን





ብፁዕ አቡነ አብርሃም እኚህ ነበሩ

በበዐለ ቂርቆስ"አዕኵትዎ ወሰብሕዎ፤ ወባረክዎ ለአብ" የሚለው እስመ ለዓለም ሲጸነነጸል በስሙ ጊዜ ሕሊናቸው ስለ ተመሰጠ የጵጵስና ልብሳቸውን እንደለበሱ ወደ ቅኔ ማኅሌት ገብተው የማኅሌቱ ተካፋይ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል ፡፡

ብፁዕ አቡነ አብርሃም በሀገረ ስብከታቸው የሚኖሩ ሁሉ በፍጹም ተዋሕዶ እምነት ሥር እንዲኖሩ እንጂ" ጸጋ ቅብዐት" የሚለው ሀሳብ እንዲቀር ይመከሩና ይገሥፁ ስለነበር "አብርሃም ነድ የቅብዐት ማቅለጫ» የሚል ቅኔ ሊቃውንት ተነግሮላቸዋል ፡፡ ከዚህም የተነሣ በዘመናቸው በተፈጥሮ ምሥጢር የማመሣጠርና የደራሲነት ተሰጦ ባላቸው ሴቶችና ወንዶች በልቅሶም ሆነ በሌላ ጊዜ ብዙ ግጥሞች ተደርሰዋል ፡፡ ከብዙ ግጥሞችም መካከል ከቅባትና ከተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በፈረቃ የቀረቡት ግጥሞች እነሆ ፡-

1. አቡኑም ተቆጡ ንጉሡም ተቆጡ፡
   ቅባቱ ቀረና ቃሪያ ሆነ ወጡ ፡፡
   (ከቅባት ወገኖች)
2. እኛ ከቅባቱ የለንም ተዘምዶ
   ቃል ሥጋ ሆነ እንጂ ከእኛ ተዋህዶ
3. ተያቸው ተያቸው ፣ ተያቸው ይለቁ
   የገዘፈን ሥጋ በቅባት ሲያረቁ (
   (ከተዋሕዶ ወገኖች)
4. የገዘፈን ሥጋ ቅባት ካረቀቀው
   በቅድመ ጲላጦስ ማን ጨርቅ አስታጠቀው" (ከቅባት ወገኖች)

**<u>ዕረፍታቸው</u>**

ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ አብርሃም ፤ ቤተ ክርስቲያንን በመምህርነት ፣ በአስተዳዳሪነት በጵጵስና በሊቀ ጵጵስና ሲያ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል

www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን



በወጣትነህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ.12 - 1)

## የጀመረውን የሚፈጽም ብፁዕ ነው

"መፈጸም እንጂ መጀመር አያቅትም" የሚል አነጋገር አለ ይህ አባባል እንደሚያስረዳው ብዙዎች ሰዎች መልካምን ነገር ለማድረግ ይነሣሉና ብዙ ርምጃ ከተራመዱ በኋላ ቀስ በቀስ ፥ እየተንሸራተቱና ርምጃቸውን እየቀነሱ የጀመሩትን ከፍጻሜ ሳያደርሱት ይቀራሉ ። ይልቁንም ዓላማቸውን ስተው የመልካም ነገር ተቃራኒ ሲሆኑ ይታያሉ ።

በመሠረቱ ይህ ወደኋላ የማለትና የመዋለል ጠባይ በማንም ሰው ላይ የሚከሰት ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ ጎልቶ የሚታየው በወጣቶች ዘንድ እንደሆነ ለመገምገም አያዳግትም ፥ ለምን? ቢባል ወጣቶች ትኩስ አስተሳሰብና ለጋ አእምሮ ያላቸው በመሆናቸው አዲስ ነገር ባዩ ቁጥር ከሚያውቁትና እነሱ ከያዙት የተሻለ መስሎ ሊታያቸው ስለሚችል ነው ። "ሁሉን ፈትኑ የተሻለውን ያዙ ከማናቸውም ክፉ ነገር ራቁ" (1 ተሰሎንቄ 5፡21) ተብሎ ተጽፏልና በርግጥ ሁሉንም ነገር አይቶ ማመዛዘን መልካም ነው ፤ ግን ትክክለኛውን ነገር ሳይገነዘቡ ወዲያና ወዲህ መዋለል በተለይ በሃይማኖት በኩል ከፍ ያለ ችግር እንደሚያስከትል መታወቅ ያለበት ጉዳይ ነው በአባቶች አነጋገር "ዘጠኝ ዳቦ ከመላስ አንዱን መንከስ" ውጤት አለው የሚባለውም ስለዚህ ነው ።

እንግዲህ ከዚህ ሁኔታ ተነሥተን በቤተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ በማገልገል ላይ ስላሉትና አገልግሎታቸውን ፥በአንዳንድ ምክንያት አቋርጠው በተለያዩ መስኮች ስለተሰማሩት ወጣቶች አንዳንድ ሁኔታዎችን ለመመልከት አመቺ መንገድ እንዲሆን ስሕተት ነው የምንለውን የተቻለንን ያህል ለመጠቆም እንወዳለን ።

ለምሳሌ ባለፉት ዘመናት ካየናቸውና ከሰማናቸው ሁኔታዎች ብንነሣ በየቤተ ክርስቲያኑ ባሉት የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት እየተመዘገቡ በጋለ ስሜት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ የነበሩ ወጣቶች ብዙዎች ሲሆኑ የትምህርት ደረጃቸውና ዕድሜያቸው ከፍ እያለ ሲሄድ ሠርተውም ገንዘብ ማግኘት ሲጀምሩ ፥ ይልቁንም በዚህ ወቅት በገንዘባቸውና በጉልበታቸው እግዚአብሔርን ማገልገል በሚችሉበት ጊዜ በልዩ ልዩ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን ይርቃሉ ይህንም በምንልበት ወቅት አንድ ወጣት የተናገረው ትዝ ይለናል ።

ወጣቱ በአዲስ አበባ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን በተቋቋመው የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ተመዝግቦ በእምነት ፈጣሪውን ሲያገለግል ከቆየ በኋላ አንድ ጊዜ የ8ኛ ክፍልን ፈተና በሚፈተንበት ወቅት በፈተናው እንዲያልፍ እግዚአብሔርን ይማፀናል ። ግን ያሰበውን ነጥብ ሳያመጣ ቀርቶ ይወድቃል። እንዳጋጣሚም በእግዚአብሔር የማያምኑ ጓደኞቹ ጥሩ ውጤት አግኝተው ፈተናውን አልፈው የሚቀጥለውን ክፍል ሲቀጥሉ እሱ ይበሳጭና እግዚአብሔርን መካድ ይጀምራል በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር መንፈስ ስለተለየው በተለያዩ ጓደኞቹ አማካይነት ልዩ ልዩ ልምዶችን ተምሮ የመጠጥ ፥ የሲጋራ ፥የፊልምና የአመንዝራነት ጠባይ ሱሰኛ ይሆናል ይህ ወጣት በአሁኑ ወቅት በአንድ መሥሪያ ቤት ተቀጥሮ በሥራ ላይ የሚገኝ ሲሆን ቀደም ሲል በተቆራኙት መጥፎ ልማዶች የሚያገኘው የወር ደመወዝ ለኑሮው እንዳልበቃው በምሬት ይገልጣል ። ከዚህም ሌላ "ምንም እንኳ ደፍሬ እግዚአብሔርን የለም ባልል እሱን ከማያምኑ ወገኖች ጋር በመተባበር በፈጸምኩት ስሕተት ጭንቀት እየተሰማኝ የመንፈስ እረፍት አጥቼ በችግር ላይ እገኛለሁ" በማለት ተናግሯል

ይህንን ለምሳሌ ያህል ጠቆምን እንጂ እያንዳንዳችን የምናውቃቸውና በምሳሌነትም የምንጠቅሳቸው ሌሎች ብዙዎች ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ ። የተነሣንበትም ዓላማ የጀመሩትን ከፍጻሜ ማድረስ ታላቅ ቁም ነገር ያለውና የሚያስመሰግንም መሆኑን በመግለጥ ጉድለቶችን ለመጠቆምና መንፈሳውያን ወጣቶቻችንን ከተሰለፉበት መንፈሳዊ ዓላማ ሳይናወጡ እስከመጨረሻው ፀንተው እንዲኖሩ ለማድረግ ነው ስለዚህ ጉድለቶች ናቸው ከምንላቸው አንዳንዶቹን ብንጠቁም የተሻለ ይመስለናል ።

1ኛ አንዳንዶች ወጣቶች የጀመሩትን መንፈሳዊ ዓላማ እየተው በመሰናከል የእግዚአብሔርን ሕልውና በመስከሩበት አንደበታቸው የክሕደት ሐዋርያት ሆነው መታየታቸው ነው ።

2ኛ ከላይ እንደተጠቀሰው ከወጣቶች መንፈሳውያን ማሕበራት ተመዝግበው ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ በየምክንያቱ እያኰረፉ ከሃይማኖት ሃይማኖት በማማረጥ የሃይማኖት ድርጅቶችን የሚያዳርሱና የወላዋይነት ጠባይ የሚታይባቸው ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ መሄዱ ነው ።

3ኛው ደግሞ በልማድ ምክንያት የሚፈጸመው ስሕተት ነው ። ለምሳሌ አካለ መጠን ያላደረሱ ወጣቶችና ሕፃናት ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበሉ ከቀረቡ የማይከለከሉ በመሆናቸው በተለይ ሕፃናት በብዛት ሲቆርቡ ይቆዩና ለአካለ መጠን በደረሱ ጊዜ ከሥጋ ወደሙ ይርቃሉ ። ወጣቶቹም ሆኑ ሕፃናቱ ሥጋ ወደሙን መቀበላቸው ተገቢና የሚደገፍም ነው ግን የምናቀርበው ጥያቄ ቢኖር በሕፃንነታቸው ጀምረው ሲቆርቡ ከቆዩ በኋላ ለአካለ መጠን ሲደርሱ ከሥጋ ወደሙ የሚርቁት ለምንድነው? የሚል ነው ።

በተለይም በየዓመቱ በጾመ ፍልሰታ ጠሙን ውሎ የሚያስቀድሰውን ሕዝብ ብዛትና ለቅዱስ ቁርባን የሚቀርቡትን ሰዎች መጠን ስንመለከት እጅግ አነሥተኛ በመሆኑና በአንፃሩም በዚሁ ጾም የሚያስቀድሱት ወጣቶች በሙሉ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል በሰልፍ የሚቀርቡ መሆናቸውን በማየታችን ይህ መንፈሳዊና ክርስቲያናዊ ተግባር መቀጠል ያለበት እንጂ አስከተወሰነ የወጣትነት ዕድሜ ተሠርቶበት ከዚያ በኋላ የሚያከትም እንዲሆን ለምን ትምህርት አይሰጥም? የሚልም ጥያቄ ለማቅረብ እንገደዳለን ።

ያም ሆነ ይህ ሰዎች ከቅዱስ ቁርባን የሚርቁት በይበልጥ በዝሙት ምክንያት ራሳቸውን ሳይተማመኑ እየቀሩ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል ይኸንም ለመገንዘብ የሚቻለው ሰዎች ለአካለ መጠን ከመድረሳቸው በፊት ያለምንም ፍርሃት ሲቆርቡ ቆይተው በኋላ እየራቁበ መሄዳቸው ነው።ሌላው ደግሞ በይበልጥ ወደ ሥጋ ወደሙ የሚቀርቡትና የሚቀበሉ ከሕፃናትና ከወጣቶች ቀጥለው ሽማግሌዎች በመሆናቸው ነው ። ታዲያ ሥጋወደሙ የሚፈተተው ክርስቲያኖች ሁሉ ተቀብለው ድህንነትን እንዲያገኙበት ስለሆነ በወጣትነታቸው ጀምረው ከመተው ይልቅ የጀመሩትን ዓላማ መፈጸም የበለጠ የሚያስመሰግን ነው ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

## ከቤተ ክርስቲያን ...

ከገጽ ፯ የዞረ

ተጠቃለው እንዲሰሩ ፤ በውጭ ሀገር

የኢትዮጵያ ምእመናን በብዛት በሚገኙባቸው ቦታዎች ኤጲስ ቆጶስ እንዲሾም ፥ በሰፈራ ፕሮግራም ለሰፈሩ ክርስቲያኖች እንደ አስፈላጊነቱ ቤተ ክርስቲያን እንዲታነጽ የተላለፈውን ውሳኔ ቅዱስነታቸው ተግባራዊ እንዲሆን አዘዋል ።

ግንቦት

21 በቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀመንበርና የኢ.ኦ.ተ. ቤ. ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ትእዛዝ 2 የሲኖዶስ አባላትና የልማት ኮሚሽን ተጠሪ በደቡብ ክፍላተ ሀገራት የደረሰውን የተፈጥሮ ችግር አጥንተው እንዲመለሱ በተደረገው መሠረት አጥንተው ተመልሰዋል ።

በኋላም ግንቦት 29 ቀን 1972 ዓ.ም በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግር ለተጐዱ ወገኖቻችን እርዳታ ለማግኘት ለዓ. አ. ክ. እና ለቅዱስ የሮማ ፓፓ የእርዳታ መጠየቂያ መልእክት አስተላልፈዋል ።

ሰኔ

22 ቀደም ሲል በቅዱስ ሲኖዶስ የተወሰነውን 38. 500(ሠላሳ ስምንት ሽህ አምስት መቶ ብር) ቅዱስነታቸው ለእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ሰኔ 21 ቀን 1972 ዓ.ም አስረክበዋል ።

—— // ——

## ይህን ያውቁ ኖሯል ?

ከገጽ ፲፩ የዞረ

የመርከብ ቅርጽ ፤ እጅግ በተራቀቀ ጥበብ የተሠሩ ልዩ ልዩ የሸክላ ዕቃዎች መንኰራኵሩ የእንጨት ሆኖ በጋማ ከብት የሚሳብ ሠረገላ ከሚስበው ከብት አጽም ጋር አብሮ ተገኝቶአል ።

ይህ እንግዲህ የዛሬ ስድስት ሺህ ዓመት ገደማ መሆኑ ነው ። ባይገርማችሁ ዛሬ እህቶቻችን ውበታቸውን ለመጠበቅ የሚያደርጉትን እንክብካቤ በዚያን ጊዜ የነበሩትም የሔዋን ልጆች ያደርጉ ነበር ። ይህንንም የሚጠቁሙ እንደ ዶቃ ፤ እንደ መስታወት ያሉ መገልገያዎች ፤ የዐይን ኩል ፤ የፊት ፡ የጥፍር ቅባት ማስቀመጫ ዕቃዎችም ከዚሁ ምድር ተቆፍረው ወጥተዋል ።

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት ቁሳቁሶች መገኘት በዚያን ዘመን የነበረው ትውልድ የሥልጣኔ ደረጃ ከፍተኛ እንደነበር የሚያስረዳ ነው ለማለት ይቻላል ።

ኅብረተሰቡ በምቾትና በተንደላቀቀ ኑሮ ሕይወቱን ይቀጭ ስለነበርም ፈጣሪውን ስለዘነጋ በልዩ ልዩ ኃጢአት ሊረክስ በቅቷል ። በንስሐ ባለመመለሱም እርሱና የገነባው ስልጣኔ እንዳልነበር ሆኖ መቅረቱን ዛሬ ከመሬት ተቆፍረው ከወጡት የከተማ ፍራስራሾች የተገኙት መዛግብትና ቁሳቁሶች ዓይነተኛ ምስክሮች ናቸው። ይህን ታዲያ

በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 24 ከቁ.37 39 ከተጻፈው የጌታ ቃል ጋር ሲያነጽሩት እንዴት ይመለከቱታል ?





www.ethiopianorthodox.org

## ሊቃውንቶቻችን ...

ከገጽ ፳፩ የዞረ

ገለግሉ ኖረው በ71 ዓመታቸው ሐምሌ 24 ቀን 1931 ዓ.ም. በሰላም ዐርፈዋል። አስከሬናቸውም በቅድስት ማርያም ቤ. ክርስቲያን አ.አ. በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል ።

### አለቃ ገብረ መድኅን

ከታወቁትና እጅግ ስመ ጥሩዎች ከሆኑት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንደኛው አለቃ ገብረ መድኅን ናቸው ። የትውልድ ቦታቸው በትግራይ ክፍለ ሀገር ነው ።

ከጐንደር ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር ተዛውረው ቅኔ ከእነ አገባቡ በሚገባ ተምረዋል ። በቅኔ ሙያም በመምህርነት ተመርቀዋል ። ሊቁ ከሕጻንነታቸው ጀምሮ ወደ መንፈሳዊ ተግባርና ወደ ፍጹማን አባቶች የሥራ ዓላማ ያተኮሩ ስለነበሩ የቅኔ ትምህርታቸውን ካሟሉ በኋላ ከጎጃም ወደ ደብረ ሊባኖስ መጡ ። በዚያም በአንድ ነቱ ገዳም ዕንጨት በመስበር ፥ ውሃ በመቅዳት ዳቤ በመጋገር ንፍሮ በመቀቀል የተራድኦ ተግባራቸውን ቀጠሉ ። ሆኖም ቤት ዘግተው ከሰው ተለይተው በገዳም ከመኖር ይልቅ የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርታቸውን አሞአልተው ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር የሚጠቅም መሆኑን ስለአረጋገጡ ሊቁ ገብረ መድኅን ከገዳማዊ ርድእና ወደ ትምህርትዓለም መዛወር ግድ ሆነባቸው። በዚህም መሠረት ወደ አንኮበር ሄዱ። በዚያም ከአለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ትርጓሜ መጻሕፍት መማር ጀመሩ። አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ የጸጋ እምነት ተከታይ ነበሩ ። በዚህም ምክንያት ሊቁ ገብረ መድኅን የጸጋን እምነት ለመከተል ስላልፈለጉ ከሥነ ጊዮርጊስ ቤት ወደ አለቃ ወልደ አማኑኤል ሄደው ትርጓሜ ሐዲሳትን በሙሉ አጥንተዋል ። በነገራችን ላይ አለቃ ወልደ አማኑኤል የወልደ አብ ወልደ ሚካኤል ደቀ መዝሙር የቡልጋ ተወላጅ ነበሩ ። እንደገናም ሊቁ ገብረ መድኅን ማን መልሶህ ወልደ ሥላሴ ከተባሉ ስመጥሩ ሊቅ የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ተምረዋል ።

አለቃ ገብረ መድኅን ለተዋህዶ እምነት እጅግ ተቆርቋሪና ቀናተኛ ነበሩ ። ከዚህም የተነሣ በዘመናቸው ማንኛውም መጽሐፈ ሃይማኖት እርሳቸው እንዲመለከቱት ይደረግ ነበር ።

ሊቁ ገብረ መድኅን በደብረ ሊባኖስ ገዳም ጉባኤ ዘርግተው በማስተማር ላይ ሳሉ ራስ አባተ ዝናቸውን ስምተው ተዋወቁአቸው ፤ በልዩ ልዩ የበጎ አድራጎት ስጦታም ይጐበኙአቸው ነበር ። ከዚህም የተነሣ ለራሳቸው ያዘጋጁትን እጀጠባብ ሱሪ ኩታ ጃኖ ካባ ሲሰጡአቸው ተቀብለው ለነዳያን አስተላልፈው ይሰጡ ነበር ። ራስ አባተ በዚህ ሁኔታ ተቀየሙ አንድ ቀንም ራስ አባተ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ቀርበው ሳሉ "አንድ ሊቅ ወዳጅ አግኝቼ ነበር ግን የምሰጠውን የትክሻዬን ልብስ ለሌላ በመስጠት አስቀየመኝ" ሲሉ ቢነግሩአቸው «አንተ ደጉን ሰው አግኝተኸዋል እንዲህ ያለ ራሱን የጠላ ሰው ከተገኘ እኔ እፈልገዋለሁ" ብለው በባለሟልነት አቅርበዋቸዋል ።

#### በደብር እልቅና

አለቃ ገብረ መድኅን አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን በመንፈሳዊ አባትነት አስተዳድረዋል ፤ ለምሳሌ ሀ የደብረ ብርሃን ሥላሴ ሸዋ ለ ገነተ ጽጌ ቅ ጊዮርጊስን አ.አ. ፤ ሐ የአደሬጢቆ ሥላሴን ሐረርጌ ፤ መ የአሰቦት ገዳምን ሐረርጌ በቅደም ተከተል ተሹመው አስተዳድረዋል ።

#### በማስተማር ያበረከቱት አስተዋጽኦ

አለቃ ገብረ መድኅን በሹመት ዕድገት ከማግኘታቸው በፊትም ሆነ በሁዋላ ከማስተማር ዓለም የተለዩበት ጊዜ አል ነበረም ይልቁንም በሹመት በነበሩበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን እያበሉና እያጠጡ እያለበሱም ያስተምሩ ነበር ። ትምህርት ቤታቸው በተማሪዎች ብዛትና በምግቡ ዝግጅት አዳሪ ትምህርት ቤት ይመስል ነበር በሌላም በኩል ዕለተ ሰንበት ካልሆነ ፀቀር እርሳቸውም ሆኑ ተማሪዎቻቸው ውለው አንድ ጊዜ ይመገቡ ስለነበር ት ቤታቸው የገዳም አቅዋም እንደነበረው ይገመታል ከደቀ መዛሙርቶቻቸው መካከል ብዙዎች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ መምህር ወልደ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር የተባሉት ግን እስካሁን በሕይወት አሉ ።

አለቃ ገብረ መድኅን ኢየሩሳሌምንና በውስጥዋ ያሉ ቅዱሳት መካናትን በዳግማዊ ምኒልክ ፈቃድ ጐብኝተዋል ። ከዚያም ተመልሰው የተለመደ ጉባኤያቸውን ቀጥለዋል ። እኒህ ሊቅ በጸሎት ኃይል በእግዚአብሔር ስም ድውይ ይፈውሱ እንደነበረ ዛሬ በሕይወት በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም (1972) የሚገኙት ደቀ መዝሙራቸው መ ወልደ ማርያም ይናገራሉ ።

አለቃ ገብረ መድኅን በድንግልናዊ ሕይወት ከኖሩ በኋላ ዕለተ ሞታቸው ሲቃረብ በደብረ ሊባኖስ ገዳም መንኩሰዋል ። ይህም የጥንታውያን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጠባይ ነው ሕይወታቸውን ሳይመረምሩ በችኮላ አይመነኩሱም ነበር ። ሊቁ የሚሞቱበትን ወር ለይተው በማወቅ ወዳጆቻቸውን እንደተሰናበቱ ይነገራል ። በ በመጨረሻም ለጊዜው በአጠገባቸው የነበሩ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን "የተማራችሁትን አስተምሩ ፤ ሃይማኖታችሁን አትለውጡ ከበጎ ምግባር አትናወጡ" በማለት መክረዋቸዋል ።

አዎ ሕይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ አንድ ቀን በሞት ጥላ ሥር ይጋረድ ዘንድ ስላለው ሊቁ መስከረም 4 ቀን 1918 ዓ.ም. በአሰቦት ገዳም ዐርፈዋል ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በደብረ ሊባኖስ ተፈጽሞአል ።

አለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ



## ልማት በቤተ ክርስቲያን

ካህናት፡— በስለት በሙዳየ ምጽዋትና በዐሥራት አስተዋጽኦ ብቻ አይኖሩም፡ ሊኖሩም አይችሉ ይሆናል ፤ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በኋላ ሊሠሩት የሚገባ ብዙ ሥራ አለ ሥራውም እንደ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ምጣኔ ሀብት ይለያያል። ለምሳሌ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ከብት ያረባሉ ። በሌላው ደግሞ የዕንጨት መሰንጠቅያና ሙሉ የቤት ዕቃዎች ማደራጃ አቋቁመው ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ለተጠቃሚ ያቀርባሉ ። እንደዚሁም መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርቶች የሚሰጡባቸው ት/ ቤቶችን ሠርተው የአካባቢውን ምእመናን ልጆች የሚያስተምሩ አሉ ። ከእነዚህም አንዳንዶችን ከዚህ በፊት በመጽሔታችን ማውጣታችን ይታወሳል ።

እነሆ በዚህ እትምም ስለ የካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናት የልማት ሥራ የደብሩን አስተዳዳሪ መልአከ ፀሐይ ታፈሰንና የሰበካ ጉባኤውን ዋና ጸሐፊ ዲያቆን ታምሩ አየነን አነጋግረናል ።



መ ፀሐይ ታፈሰ

ትንሣኤ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስትያን በአሁኑ ጊዜ በአካባቢዋ አንዳንድ ልማቶችን እያቋቋመች ራስዋን በራስዋ ለማስተዳደር ሙከራ በማድረግ ላይ ትገኛለች በዚሁ መሠረት በደብረ ሣህል ቅ/ሚካኤል ምን አይነት ልማት አቋቁማችሁአል?

መልአከ ፀሐይ፡- አዲስ መመሪያ በቃለ ዓዋዲው ከወጣ ጀምሮ በርከት ያሉ የልማት እንቅስቃሴዎች ይካሄዳሉ ። ለምሳሌ ከለውጡ ወዲህ፡- የቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረት በአስፋልት ተነጥፎአል ። የቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ጠባብ ስለነበር ሰፊ ሆኖ እንዲሠራ ተደርጎአል ። ቤተ ልሔሙ በዘመናዊ አሠራር ተሠርቶአል እንደዚሁም ልዩ ልዩ ቅርሳቅርሶችንና ንዋያተ ቅድሳትን በጥሩ ሁኔታ ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ ትልቅ ቤት ተሠርቶ በአገልግሎት ላይ ይገኛል ። ይህ ሁሉ እኔ ከመምጣቴ በፊት የተፈጸመ የሥራ ውጤት ነው ።



የዳቦ መጋገሪያው ክፍል

እኔ በአስተዳዳሪነት ወደ የካ ደብ፡ ሣህል ቅ/ሚካኤል ከመጣሁ ወዲህ ደግሞ የአካባቢው የቀበሌ ማኅበራት ባደረጉት ትብብር የሀገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር ስለ ፈቀደልን የቤተ ክርስቲያኑ የግል በሆነው ቦታ ላይ 1ኛ የዳቦ መጋገሪያ 2ኛ/ት/ቤት ተቋቁሞ አገልግሎቱን ጀምሮ አል ። ካህናቱም ራሳቸውን ለመርዳት እላይ በተጠቀሱት አነስተኛ እንዱስትሪዎች ውስጥ በትጋት ይሠራሉ ። ይህ እንቅስቃሴ ወደ ፊት ለቤተ ክርስቲያኑ መጠነኛ ገቢ የሚያስገኝ ከመሆኑም ሌላ የአካባቢውን ተመጋቢ ሕዝብ ችግር በመጠኑ እንዲሚያቃልል ተስፋ ይጣልበታል ።

ትንሣኤ፡-በትምህርት ቤቱ ምን አይነት ትምህርት ይሰጣል?



የቄግ መምህሩ በግስተግር ላይ ሳሉ



የቅኔው መምህር ቅኔ ሲያስነግሩ

ዲያ.ትአምሩ፡- በመሠረቱ ት/ቤቱ 4 ክፍሎች ሲኖሩት አራት የትምህርት አይነቶች ይሰጡበታል ።

እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ/ መሠረተ ትምህርት ከፊደል እስከ ወንጌል

2ኛ/ የመጻሕፍት ትርጓሜ ቅኔ /ግዕዝ/

3ኛ ጽዋተወ ዜማ

4ኛ የቅዳሴ ዜማ

ወደፊት ግን ዘመናዊ ትምህርትም እንዲሰጥባቸው ለማድረግ ዕቅድ አለን ።



www.ethiopianorthodox.org

ትንሣኤ፡-የመምህራኑና የተማሪዎች ብዛት ምን ያህል ነው?

ዲ.ተአምሩ፡- መምህራኑ አራት ናቸው ። የተማሪዎችም ብዛት አንድ መቶ ያህል ነው

ትንሣኤ፡-ለወደፊት ያላችሁ ዕቅድ ምንድን ነው?



ሊ ዲያቆን ታምሩ አየለ

መልአከ ፀሐይ፡- ለወደፊት የምንሠራቸው አንዳንድ ዕቅዶች አሉን። ከእቅዶቹም መካከል አንዱ የቅዱስ ሚካኤል ጽላት ስለነበረበት ጥንታዊ ዋሻ ይሆናል የዚህን ታሪካዊ ዋሻ ሁኔታና ለወደፊትም ያለውን የሥራ ዕቅድ ዝርዝር የሚገልጽ አጭር ጽሑፍ በመጽሔት መልክ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ በመዳረስ ላይ ነው ፡ ሁለተኛ በፀበሉ አካባቢ ቤተ ሕሙማን ለመሥራት ዕቅድ አለን ብለዋል ።

ከአዘጋጅ፡- "ጥርስና ከንፈር ቢደጋገፍ ያምር" እንደሚባለው በደብሩ ያለው መንፈሳዊ ትብብር ጥሩ ነው ካህናቱ ከአስተዳዳሪውና ከሰበካ ጉባዔው ጋር ያላቸው ትብብርና አንድነት ጠንካራ በመሆኑ የተጀመረው ሥራ ተፈጽመዋል በውጥን ያሉትም አንዳንድ ሥራዎች በእግዚአብሔር አጋዥነት የሚያግድ ኃይል አይኖርምና ይፈጸማል ።

ከላይ የተዘረዘሩትን የልማት እንቅስቃሴዎች ለማካሄድ እንዲያመችም አዲስ በወጣው ቃለ ዓዋዲ ም4.ቁ1 በፊደል "ሠ" በተመለከተው መሠረት የልማት ኮሚቴ ተቋቁሞ እንደነበረና ተመራጮችም በጥቃቅን ምክንያቶች ለመሥራት ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ሥራውን ለመጐተት ሞክረው እንደነበር እናስታውሳለን ። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያኑ ኃላፊነት የተጣለባቸው የሰበካ ጉባዔ አባላትና ካህናቱ በመተባበር የልማቱ እንቅስቃሴ ግቡን ሊመታ ችሏል ።

በደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የተቋቋሙት ልማቶች ታላቅ ተስፋ የሚጣልባቸውና ለሌሎችም አ አብያተ ክርስቲያናት ምሠረታዊ አርአያ እንደሚሆኑ አያጠራጥርም።በተለይ መልአከ ፀሐይ ታፈሰ ደሳለኝ እንደገለጹልን ት ቤቱና የዳቦው መጋገሪያ የተሠሩበት ቦታ የበጎች ማጐሪያ ከመሆኑ የተነሳ ለማየት የሚያጸይፍ ለአፍንጫ የከረፋ ነበር የቤቱም ክዳን ሣር ስለነበር ሣሩ በስብሶ በአጠገቡ ለማለፍ የማይቻል እንደነበር አብራርተውልናል ።

ግን በዚህ መልክ የነበረውን ቦታ ቆሻሻውን ጠርገው አካባቢውንም አጽድተው የእግዚአብሔር ቃል የሚነገርበት መንፈሳዊ ጥበብም የሚቀሰምበት ማድረጉ በቀላሉ የሚገመት አይደለም"ሰብእ ይቄድሶ ለመካን" የሚለውም ዘይቤ ተገቢውን ትርጉም አግኝቷል ።

እንግዲህ ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት የዚህ ዓይነት ዕድል እንዲገጥማቸው እየተመኘን የደብር አለቆችም ይህን ለመሰለውና ከዚህ ለበለጠ የልማት ሥራ ቢተጉ መልካም ነው እንላለን ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

//

# የአብያተ ክርስቲያናት ዜና

### የአስቸኳይ ርዳታ ተጠየቀ

**አዲስ አበባ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያርክ በኢትዮጵያ የደረሰው ድርቅ ያስከተለውን ችግር በመግለጽ የአስቸኳይ ርዳታ ጠየቁ ግንቦት 24 ቀን 1972 ዓ.ም የተሰበሰበው ቅ ሲኖዶስ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ከቅ ሲኖዶስ የተውጣጡ አባላት ያሉበት አጥኚ ቡድን ድርቁ ወደ አጠቃቸው የደቡብ ክፍላተ አህጉር ሄዶ አጥንቶ ተመልሷል ። ቡድኑ ያቀረበውን ጥናት ቅ ፓትርያርኩ ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የአስቸኳይ ርዳታ ሰጪ ክፍልና ለሮማ ጋጋ አስተላልፈዋል ።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም በሀገራችን የደረሰውን ድርቅ በማስመልከት ለልዩ ልዩ ርዳታ ሰጪዎች ጥያቄአቸውን መላካቸው ታውቋል ።

**ቶሮንቶ**

ዝምባብዌ ለልማት ርዳታ ልታገኝ ነው ።

ግንቦት 26-28 ቀን 1972 ዓ.ም የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን የልማት ክፍል በካናዳ ዋና ከተማ ቶሮንቶ ላይ ተሰብስቦ በ12 አፍሪካ በ6 ኤስያ በ6 አሜሪካ አገሮች ለተቋቋሙ 24 የልማት እቅዶች 12 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ርዳታ ለመስጠት ወሰነ ።

ከዚህ ርዳታ ውስጥ 4.6 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ለዝምባብዌ ልማት ለተግባረ ዕድ ፣ ለማኅበራዊ ኑሮና ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል መሆኑን የፌዴሬሽኑ ሳምንታዊ ጋዜጣ በ23 80 ኛ ቁጥር ገለጠ ።

**ሎንዶን**

የዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ማደራጃና ማሰራጫ ማኅበር ከግንቦት 23 እስከ ሰኔ 1 ቀን 1972 ዓ.ም በሎንዶን ከተማ ተሰብስቦ ከ51 አገሮች ከኦርቶዶክስ ፣ ከካቶሊክና ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የቀረቡትን 115 ፕሮግራሞችንና እቅዶችን እ.አ.አ. ለ1981 ከ5.6 ሚሊዮን የኢ.ትዮ.ብር በላይ ማጽደቁ ተገለጸ ። ርዳታው የሚሰጣቸው የመገናኛ ዘዴዎችን በማደራጀትና በማሰራጨት ላይ ተሰማርተው ለሚሠሩ በአፍሪካ ለ31፣ በኢሲያ ለ30፣ በላቲን አሜሪካና ካረቢያን ደሴቶች ለ25 በመካከለኛው ምሥራቅ ላይ በፓስፊክ ደሴቶች ለ8 በኤሮፓ ለ5 አብያተ ክርስቲያናት መሆኑ በተጨማሪ ተገልጧል ። ዳሉ ተገለጸ ።

**ጀኔቭ**

በምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት ሀገሮች ከ102 ሚሊዮን በላይ ክርስቲያኖች እንዳሉ ተገለጸ

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ጽ/ቤት በአባላት አብያተ ክርስቲያናት ያሉትን የምእመናን ብዛት ለማወቅ ባወጣው ስታስቲክ መሠረት በምሥራቅ አውሮፓ በሁንጋሪያ ፣ በመላዋ ሩሲያ ፣ በቸኮዝላቫኪያ ፣ በምሥራቅ ዲሞክራቲክ ጀርመን ፣ በፖላንድ ፣ በሩማንያ፣ በዩጎዝላቪያና በቡልጋርያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ያሉአቸው የምእመናን ብዛት የተለያዩ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት 88.680.000፣ የባፕቲስት ቤተ ክር 1.120.500፣ የተለያዩ የሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት 9.180 087 ፣ የጥንታዊት ካቶሊክ 49.293 ፡ የፕሬስ ቢተርያን 3.175.227 በድምሩ 102.205.107 ቀዋሚ ምዕመናን እንዳሉአቸው ተገልጾአል ። ይህም ቁጥር በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በአባልነት የተመዘገቡትን የአብያተ ክርስቲያናት ተከታዮች ብቻ የሚጠቁሙ መሆኑ ግልጽ ነው ።

**ማድራስ ሕንድ**

በሕንድ ያሉ የኦርቶዶክስና ሉተራውያን የሃይማኖት ምሑራን የመቀራረቢያ ውይይት አደረጉ ።

እንደ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አገላለጽ ጥንታዊነት ያላት የሶሪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነበረች በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በሶሪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በተደረገው ለውጥ መሠረት በማርዞማ የሶሪያ ቤተ ክርስቲያን ፣ በማልንካር ያዕቆባዊት የሶሪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከአንጾኪያው መንበረ ፓትርያርክ ሥር ያለችውና ጥቂት ተከታዮች ያሏት ኪልቂደናዊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲሆኑ አንድ ሚሊዮን ተከታል አባላት አሉአቸው ፕሮቴስታንቶች ደግሞ አንድ ሚሊዮን አባላት አሉአቸው ።

ውይይቱ የተካሄደው በኦርቶዶክስና በሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት የዕምነት ምሑራን መካከል ነበር። የተጀመረው በ1969 ዓ.ም ተሰብስበው ባጸደቁት መርሐ ግብር መሠረት አሁን ያሉበትን ሁኔታ ፣ የቅርሳ ቅርስ ሀብት በአብያተ ክርስቲያናት አጠቃቀምና አጠባበቅ በግልጽ ከመወያየታቸውም ሌላ የሥርዓተ አምልኮትና የመንፈሳዊ ትምህርት አቋም የሚያመለክቱ ነበሩ ። ውይይቱ ለሁለቱ የሃይማኖት ድርጅቶች ለጋራ ጥቅም ተፈላጊ በመሆኑ የሕንድ አብያተ ክርስቲያናት ተልኮአቸውን ለማሟላት መንገድ ጠራጊ ነው ።

በምሁራኑ ከቀረቡት የመንደርደሪያ ሃሳባት መካከል

1. ፍትህ ከእምነትና ከማኅበራዊ ኑሮ ጋር ያለው ዝምድና ፣ 2. የድንግል ማርያም ክብር በቤተ ክርስቲያን 3. ባህልና የወንጌል መልዕክት ፡ 4. ባለሥልጣኖች በቤተ ክርስቲያን 5. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን 6.ቤተ ክርስቲያን ከክርስትና ውጪ ከሆኑት ሃይማኖቶች ጋር ያላት ዝምድና ። 7.የሉተራውያን አግስበርግ አንድነት ማኅበር በዛሬዋ ሕንድ የሚሉ ነበሩ ።

በነዚህም የመንደርደሪያ ሀሳቦች ላይ ሉተራውያንና የኦርቶዶክስ ምሑራን በየበኩላቸው ወደ ስምምነት ተቃርበዋል ።

የሚቀጥለው ስብሰባም ከሕዳር 22-25 ቀን 1973 ዓ.ም በጉሩኩል መንፈሳዊ ኮሌጅና ጥናትና ምርምር ተቋም በኪልፓውክ ከተማ በማድራስ ይደረ ሥርዓተ እምነትና ቅዳሴ ፣ የቤተ ክርስቲያን ዓላማዎችና ፈጻሚዎቻቸው እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንና የእግዚአብሔር መንግሥት የሚሉ ይሆናሉ

በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በሥርዓተ አምልኮት አፈጻጸምና በሥርዓተ ቅዳሴ ሰፋ ያለ ልዩነት እንዳላቸው ግልጥ ቢሆንም ባለፉት ውይይቶች ሰፋ ያለ መግባባትና የመቀራረብ ውጤት ታይቶአል ።በአንድነት ተሰብስበው ለሥርዓተ ጸሎት ተሰልፈው መታየታቸው በክርስቶስ ለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን አንድነትና የመጀመሪያ መንገድ ጠራጊ ጉባኤ መሆኑን የሉተራውያን ሳምንታዊ ጋዜጣ በ23/80ኛ ቁጥር ገለጠ ።

//

## ክርስቲያንና ተግባሩ

ከገጽ ፳ የዞረ

4ኛ ለሕይወታችን በምናዘጋጀው መንፈሳዊ ዝግጅት ክርስቲያንነታችንን ለሌሎች ልናስታውቅ እንችላለን ።

በአለባበስ በኩል የተመለከትን እንደሆነ ሰው ከልቤ እንጂ ከልብሴ ምን አለው የምትሉ እንዳላችሁ ተሳስታችኋል ። በእርግጥም የልብስ አለባበስ ሁኔታ ለብዙ ችግርና ፈተና ጭምር ሊሆን ይችላል ። ምክንያቱም የክርስቲያኖች አለባበስ ወደ ዝሙት የሚስብና የሚማርክ ሳይሆን በተቻለ መጠን በጣምም የማያሳጣ ደግሞም የዘመኑን ቅጽ ተከትሎ ከየእለቱ ሁኔታ ጋር የማይለዋወጥ ልብስ ለመልበስ መሞከር ለሌላው ጥሩ ምሳሌ ለመሆን ያስችላል እግዚአብሔር በተፈጥሮ ሁሉንም አደላድሏልና ።

በአነጋገርም በኩል የሄድን እንደሆነ የክርስቲያኖች አነጋገር ከሌሎች ሰዎች አነጋገር የተለየ ሊሆን ይገባል ይኸውም





www.ethiopianorthodox.org

ከክርስቲያኖች እንደበት የሚወጣውን የሚጠባበቁ ብዙ ሰዎች ስላሉ የምናወራው ለትዝብት እንዳያውለን ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል ። መነገር የሌለባቸው ታሪኮችና ቀልዶች አናውራ ለመማል ወይም ለመርገምና ለመሳደብ ለአንደበታችን ነጻነት አንስጠው ሌላው ቀርቶ ንዴታችንና ብስጭታችንን እንኳን ለመደበቅና ላለማሳየት ብንሞክር ጥሩ ነው ከሁሉም ይልቅ ደግሞ አንዳንድ ክርስቲያኖች የምንጠመድበት ፈተና የሐሜት ፈተና ነው ። ይኸውም በየመንገዱ ፣ በየማዕዘኑ ፣ በየቤቱ ሁሉ መልካም ተብሎ የተደነቀው ስም ሲዋረድና ሲታማ ይሰማል ። ክርስቲያኖች ከዚህ በሽታ ፍፁም ነፃ ለመሆን መጣጣር አለብን ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ክርስቲያኖች ምክሩን ሲለግስ "ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን" ብሏል። (ቆላሳይስ 4:6)

ለምሳሌ አልፎ አልፎ ጓደኞቻችን መጥፎ ነገር ሲያወሩ ለመስማት እንገደድ ይሆናል ። ግን ነገሩ መጥፎ መሆኑን ካስተዋልን ባንተባበራቸው የሚወቅሰን የለም የሰማነውንም መጥፎ ወሬ ሁሉ ለሌላ አልፎ አለመንገር ያስመሰግናል ሐዋርያው እንዳለው ነገራችን ሰዎችን የማያስቀይም ሊሆን ይገባዋል ። ይህ ከሆነ ክርስቶስ በልባችን ስለሚያድርና ሥራችንም የተስተካከለ ስለሚሆን ከአንደበታችን መልካም ቃላት ብቻ መውጣት አለበት ። ስለዚህ ንግግራችን ሁሉ ሌላውን የሚያርም ፣ የሚያንጽ እንዲሆን ያስፈልጋል ።


አካሄዳችንም ክርስቶስን የሚያስከብር መሆን አለበት አንድ መዝሙረኛ ሲዘምር "ትናንሺ እግሮች ሆይ አጉል ቦታ እንዳትትወስዱኝ ተጠንቀቁ" ብሏል ። ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ይህንን ምክር ለእያንዳንዱ የሰውነት ክፍሉ መስጠት ይገባል ። ስለዚህ የክርስቲያን እጆች ፣ ዓይኖችና ጆሮዎች ሁሉ ከክፉ ቦታ መራቅ አለባቸው ። ተግባር ከቃላት ይልቅ ይናገራል ይባላልና የክርስቲያን አካሄድ ሁሉ በተግባር ካልሠመረ ከአንደበቱ የሚወጣው ምስክርነት ሁሉ በሌላው ዘንድ ተሰሚነት አያገኝም ። በተለይም በምንሠራበት መሥሪያ ቤት ሁሉ ለሌሎች ጥሩ ጠባይ ማሳየት ይፈለግብናል ። ለምሳሌ የሥራ ጓደኞቻችን በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ስለማይተባበሩን ይጠሉንና ያፌዙብን ይሆናል ። ይሁን እንጂ መገንዘብ ያለብን ደስታና ሰላም የመላበት የክርስቲያኖች አካሄድ እስከ መጨረሻ ድረስ ከቀጠለ ሰዎችን እያስቀና ወደ መልካም ተግባር ሊስባቸው ይችላል ። ምንጊዜም ቢሆን መልካም ሥራ ያለምንም ቅራኔ ያለ ጥል ፣ ያለክርክርና ፣ ያለ ጸጸት በክርስቶስ የሚገኘው ጸጋ ዓለማዊውን እንደማረከውና እንዳስቀናው ይኖራል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ወደ መዝናኛ ሥፍራ ካልሄድን እንዴት ለመደሰትና ሰላም ለማግኘት እንችላለን ብለን እንጠይቅ ይሆናል ።ኢሳኢያስ በምዕራፍ 30 ቁጥር 21 "ዓይኖችህ ግን አስተማሪህን ያያሉ ፣ ወደ ቀኝም ወደግራም ፈቀቅ ብትል ጆሮችህ በኋላህ መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ" ይላል እንዳለውም ለህይወቱ ግብ አበጅቶ ጉዳናውን በተወሰነ አቅጣጫ የማይቀይስ ክርስቲያን ሕይወቱ ትመሰቃቀልበታለች ። ስለዚህ የትም ቢገባ ምንም ሥራ ቢሠራ ከዓላማው ሁሉ አንደኛው ስለ ክርስቶስ መመስከር ነው ። የእግዚአብሔር መንገዶች ሁሉ ቅን ናቸው ። ከትእዛዙም የማይወጣ አይሰናከልም ተብሏልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በትንሣኤ መጽሔት ቁ. 33 ላይ በወጣው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር አሸናፊዎች በመሆን 3 ሰዎች ሽልማት ተቀብለዋል ። እነርሱም 1ኛ. አቶ ሕዝቅያሳ ዝቁ ፣ 2ኛ. አቶ ዓለማየሁ ጉልላትና ወታደር እርጋው መኩርያ ናቸው ።


አቶ ሕዝቅያስ ዝቁ


አቶ ዓለማየሁ ጉልላት


ወ ር አራጋው መኩሪያ




# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር

የተወደዳችሁ የትንሣኤ መጽሔት አንባቢያን ፡

በሰኔ ወር 1972 ዓ.ም. ባቀረብንላችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ውድድር ብዙዎቻችሁ እንደተደሰታችሁ በላካችሁልን አስተያየት ለመረዳት ችለናል ። ከአስተያየቶቻችሁም ለመረዳት እንደቻልነው ፡ቀድሞ እንደምናደርገው የንባብ ክፍል ብቻ በዚህ አምድ ከምናቀርብላችሁ ይልቅ ፡ በየጊዜው የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር ብናቀርብ የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ለማጥናት የሚገፋፋችሁና የሚረዳችሁ እንደ ሆነ ተገንዝበናል ። እኛም ይህንኑ ለመቀጠል ደስታችን እንደሆነ ልንገልጽላችሁ እንወዳለን ፡ ስለዚሁ ጉዳይ የብዙዎችን አንባቢያን አስተያየትና ፍላጎት ማወቅ ስለምንፈልግ ጻፉልን ። የዚህ ውድድር አሸናፊዎች ሽልማት ወደፊት ይገለጣል ። ለዛሬው ያዘጋጀንላችሁ ውድድሮች እነሆ ፡

1. ሥጋዊ ሞትን ሳይቀምሱ እግዚአብሔር የወሰዳቸውን ቅዱሳን ስም ግለጽ ።
2. አቤልና ኖህ በእምነታቸው ያተረፉት ተመሳሳይ ባሕርይ ምን ነበር?
3. እግዚአብሔርን ለማስደሰት ያስቻሉት ሁለቱ የአብርሃም መልካም ባሕርያት ምን ምን ናቸው?
4. አብርሃም በሕይወቱ ሁሉ ይጠብቀው የነበረውስ ተስፋ ምን ነበር?
5. ሙሴ በእምነት የወሰደው ርምጃ ምን ነበር?
6. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ታሪካቸው እንደተገለጸው ፡- የጠፋው በግና ድሪም እንዲሁም የአባካኙ ልጅ መመለስ ምንን ያመለክታሉ ?
7. የዕብራውያን ምዕራፍ 11 ቁጥር 39-40 ሃሳብ ምን ማለት ይመስልሃል?
8. ይህ ታሪክ የተፈጸመው በአዲስ ኪዳን ነው ። የማን እንደሆነና ድርጊቱን አስረዳ ።



የጐደሉትን ቃላት ሙላ ፡

9. እኛ ግን ——— ——— እንሰብካለን ።
10. የእግዚአብሔር ——— ሕያው ነውና ።
11. ቃሉን ——— ሁኑ እንጂ ——— እያሳታችሁ ——— ብቻ አትሁኑ ።
12. ዕረፉ እኔም ——— እንደሆንሁ ——— ።

ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልሱ የሚገኝበትን መጽሐፍ ፣ ምዕራፍና ቁጥር ስጥ ።

ባለፈው ውድድር አንዳንዶቻችሁ እንደገለጻችሁልን መጽሔቷ ዘግይታ ስለምትደርሳችሁ ጊዜው እንዲራዘምላችሁ ጠይቃችኋል ። ለወደፊቱ መጽሔቷ እስከወጣችበት ወር መጨረሻ መልሳችሁ ቢደርስ እንቀበላለን ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
የመ.ሣ.ቁ. 1252
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org